መግቢያ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ዋና ኦዲተር መ/ቤት በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 116/2 እና መ/ቤቱን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 186/2003 እና 267/2011 መሠረት፣ በክልሉ የሚገኙ የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ለመደበኛ ተግባራትና ለካፒታል ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የተመደበላቸውን በጀት በፋይናንስ ሕግ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን፤ የገንዘብና የንብረት አስተዳደራቸው ሕግ፣ደንብና መመሪያን የተከተለ መሆኑን፣ ከምዝበራና ብክነት መጠበቁን ለማረጋገጥ የክልሉን የቆዳ ስፋት፣ የአወቃቀር እርከንና የሴክተር አደረጃጀት፣ለየመ/ቤቱ እንዲሁም ለመ/ቤታችን የተመደበውን በጀት፣ ያለውን የሰው ኃይል እና ሌሎች ተጨባጭ ሁኔታዎችን ከግንዛቤ በማስገባት አጠቃላይ ተቀባይነት ያላቸውን የኦዲት ደረጃዎችና የአሠራር ሥርዓቶችን በመከተል ያከናወናቸውን ተግባራት ያካተተ አጠቃላይ ዘገባ በዚህ ጥራዝ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሠረት የተጠቃለለው ውጤት እንደሚያመለክተው፡-

1. መ/ቤቱ ከጥር 1/2013 እስከ ግንቦት 30/2014 ዓ/ም ባሉት ወራት የ256 መ/ቤቶችን የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ለማድረግ አቅዶ የ138 (54%) መ/ቤቶች ኦዲት ተከናውኗል፡፡ የሁሉም መ/ቤቶች ኦዲት ውጤት በዚህ ሪፖርት ተጠናቅሮ ቀርቧል፡፡
2. የ2013 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በአወቃቀር እርከን ሲታይ በክልል/ማእከል 40(29%)፣በዞን 6(4%)፤በከተማ አስተዳደሮች 34(25%) ቀሪዎች 58(42%) በወረዳ ደረጃ ያሉ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ የኦዲት ሽፋን በእስትራቴጅካዊ ዘመኑ ቅድሚያ እንዲያገኙ ከተለዩት 776 ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ቁጥር አንፃር ሲታይ 17.78% የደረሰ ሲሆን የኦዲት ሽፋኑ ከበጀት አንጻር ሲታይ ደግሞ አጠቃላይ ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች የበጀት ወጪ ብር 19,080,359,487.26 በመሆኑ ለ2013 በጀት ዓመት በክልሉ ምክር ቤት ከታወጀው ብር 62,698,672,937.00 አኳያ ሲታይ 34% እንዲሁም ከገቢ በጀት አንፃር ሲታይ አጠቃላይ ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች የገቢ በጀት ብር 4,737,097,927.60 በመሆኑ በ2013 በጀት ዓመት ክልሉ በራሱ አቅም ለመሰብሰብ ከአቀደው የገቢ በጀት ብር 24,147,723,000.00 አኳያ ሲታይ 20% የኦዲት ሽፋኑ መድረሱን ያሳያል፡፡
3. ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብትና ሰነዶች፣ የሂሳብ መግለጫዎች እንዲሁም በየደረጃው ያሉ የሚመለከታቸው ሰራተኞች እና ኃላፊዎች የሠጧቸው ማብራሪያዎች ናቸው:: ከዚህም በተጨማሪ ከ3ኛ ወገን የተገኙ ብቃትና ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች ሥራ ላይ ውለዋል::
4. የመ/ቤቶቹን ሂሳብ ኦዲት ማድረግ የመ/ቤታችን ኃላፊነት ሲሆን የሂሣብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት፣ ኦዲት የማስደረግና የሠሩበትን ዝርዝር ሁኔታ የማስረዳት እንዲሁም በኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ እርምጃ መውሰድ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኃላፊነት ነው::

5. የኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶች ከጥሬ ገንዘብ፣ከገቢ፣ከተሰብሳቢ፣ከወጪ፣ከተከፋይ፣ከሂሣብ ሪፖርቶችና ከንብረት አስተዳደር ኦዲት የተገኙ ሲሆኑ በዚህ ሪፖርት በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

   በበጀት ዓመቱ በድምሩ ብር 4,310,659.09 የገንዘብ ጉድለት፣ማጭበርበር የተከሰተ እና ለግል ጥቅም የዋለ ሲሆን መ/ቤቶችም እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

   - የጃናሞራ ወረዳ የወይና ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት ብር 908,318.74፣ከለላ ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ብር 901,919.04፣አብክመ ቤቶች ልማት ድርጅት ብር 583,625.00፣አብርሀ ጅራ የመጀመያ ደ/ሆስፒታል ብር 542,917.50፣የመተማ ከተማ ሆስፒታል ብር 309,960.00፣ተንታ ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ብር 130,562.63፣ጃቢ ጠህናን ወረዳ ፍ/ቤት ብር 139,826.54፣የስማዳ ወረዳ የየኳሳ 1ኛ ደ/ት/ቤት ብር 117,074.69፣በየዳ ወረዳ ውሃ መስኖና ኢነርጅ ልማት ጽ/ቤት ብር 99,011.71፣የአምቦ ሜዳ ንዑስ ማዘጋጃ ቤት ብር 80,888.72፣እብናት ወረዳ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል ብር 79,473.45፣አብርሀ ጅራ አጠ/2ኛ/ደ/ት/ቤት ብር 73,778.83፣የጣና ክፍለ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ብር 69,180.94 ፣በእንሳሮ ወረዳ ልጅ ስዩም ገ/ህይወት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ብር 56,643.52፣ባሶ ሊበን ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ብር 49,930.24፣መካነ ሰላም ጠቅላላ ሆስፒታል ብር 49,425.26 ፣ የአማራ ህዝብ ዝክረ ታሪክ ማዕከል ብር 45,755.96፣ባህር ዳር ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 42,850.00፣ሙሉ ዓለም የባህል ማዕከል ብር 16,983.54 ፣ውጫሌ ከተማ መሪ መዘጋጃ ቤት ብር 12,532.78፣ ናቸው፡፡

6. በዚህ አጠቃላይ ዘገባ ለየመ/ቤቱ ከተላከው የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ሪፖርቶች ዝርዝር ተለቅመው የተጠቃለሉ ግኝቶች እንዲሁም ከ2009 እስከ 2013 ባሉት 5 ዓመታት በተከናወነ ኦዲትና በተዘጋጁት የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት አዝማሚያውን ለማሳየት የዋና ዋና ግኝቶች አማካይ ውጤት በግራፍ ተደግፎ ቀርቧል፡፡ የዚህ ሪፖርት ዋና ዓላማ የክልሉ ምክር ቤት የበጀትና መንግስት ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ የርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤትና ሌሎችም የሚመለከታቸው አካላት ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶችን ግኝቶች በመገምገም የፋይናንስ፣ ግዥና ንብረት አስተዳደሩን አጠቃላይ ሁኔታዎች ለማሻሻል ለሚደረጉ ውሳኔዎች እንዲጠቀሙበትና ተጠያቂነትንም ለማጠናከር በማሰብ የቀረበ ነው፡፡

7. የሪፖርቱ አቀራረብ የ2013 በጀት ዓመት ሂሣብ የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ውጤት፣ ያለፉት ዓመታት የኦዲት ውጤቶች እርምጃ አወሳሰድ የክትትል ኦዲት፣ያለፉት አምስት ዓመታት አፈጻጸም አዝማሚያ ትንተና ማጠቃለያና የማሻሻያ አስተያየት በቅደም ተከተል ከምዕራፍ 1-4 በማካተት ሲሆን ለሪፖርቱ ደጋፊ አባሪዎች -------ገጽ በሪፖርቱ መጨረሻ ተያይዘዋል፡፡

ምዕራፍ -አንድ

1. የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ዕቅድ አፈፃፀም፣

1.1. የኦዲት ሽፋን፣

1.1.1. የኦዲት ሽፋን በክልል/ማዕከል፣በዞን ከተማ እና ወረዳ ደረጃ፣

በበጀት ዓመቱ ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በያልል/ማዕከል፣ዞን ፣ከተማ እና □ረ□ ደረጃ የተያዘው ዕቅድና አፈፃፀም በንጽጽር ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ-1 የኦዲት ሽፋን በክልል/ማዕከል፣ወረዳ፣ከተማ እና ዞኖች ከ2012 ክንዉን ጋር በንፅፅር

ተ.ቁ	ዞናዊ ስርጭት	የ2012	የ2013		ንጽጽር	
		ክንውን ብዛት	ዕቅድ ብዛት	ክንውን ብዛት	ከዓመቱ ዕቅድ%	የ2013 ከ2012 ክንውን%
1	የያልል /ማዕከል / መ/ቤቶች	**102**	78	**40**	51	-60
2	ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር	**5**	3	**3**	1	-40
3	ምዕራብ ጎጃም	**25**	22	**12**	55	-52
4	ምስራቅ ጎጃም	**16**	30	**21**	70	31
5	ማዕከላዊ ጎንደር	**4**	16	**9**	56	125
6	ሰሜን ጎንደር	**9**	10	**6**	60	-33
7	ምዕራብ ጎንደር	**1**	4	**2**	50	100
8	ደቡብ ጎንደር	**16**	31	**17**	55	6
9	አዊ ብሔ/አስተዳደር	**12**	22	**12**	55	0
10	ሰሜን ወሎ	**26**	5	**0**	0	-100
11	ደቡብ ወሎ	**40**	14	**7**	50	-83
12	ሰሜን ሸዋ	**30**	15	**8**	53	-73
13	ዋግኽምራ ብሔ/ አስተዳደር	**8**	2	**1**	50	-88
14	ኦሮሞ ብሔ/አስተደደር	**7**	**4**	**0**	0	-100
	ድምር	**301**	**256**	**138**	54	-54

- የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ክንውን ካለፈው በጀት ዓመት አፈፃፀም ጋር ሲነፃፀር በ163 መ/ቤቶች የቀነሰ ሲሆን የቀነሰበትም ምክንያት በክልሉ በአጋጠመው የፀጥታ ችግር ምክንያት የክልሉ መንግስት በአወጀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ምክንያት ከአስገዳጅ የኦዲት ስራዎች በስተቀር የኦዲት ስራ ማከናወን ባለመቻሉ ነው፡፡

1.1.2. የኦዲት ሽፋን በአወቃቀር እርከን፤

የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ ክንውን በአወቃቀር እርከን ሲታይ እንደሚከተለው ነው፡፡:

ሠንፀረዥ-2 የኦዲት ሽፋን በአወቃቀር እርከን

ተ.ቁ	የአወቃቀር እርከን	2013 ሂሳብ ኦዲት ክንውን	
		በመ/ቤት ብዛት	ከጠቅላላዉ ክንዉን በ%
1.	ያልል/ማዕከል	40	29
2.	ዞን አስተዳደር	6	4
3.	ወረዳ አስተዳደር	58	42
4.	ከተማ አስተዳደር	34	25
ድምር		138	100

1.2. የኦዲት ስልት:-

የ2013 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ከጥር 1/2013 እስከ ግንቦት 30/2014 በጀት ዓመት ኦዲት ከተደረጉት 138 መ/ቤቶች ውስጥ 100(72%) በንሞና እንዲሁም 38(28%) መ/ቤቶች የልዩ ኦዲት ጥቆማና ጥያቄ ቀርቦባቸው በየነጥቦቹ መነሻ መሠረት በዝርዝር ኦዲት የተደረጉ ናቸዉ፡፡

የኦዲት ሥራውን በአብዛኛ ው በመደበኛው እና በንሞና የኦዲት ስልት ለማከናወን ታቅዶ 72% በንሞና የኦዲት ዘዴ ኦዲት የተደረገ ሲሆን የኦዲት ሥልቱ ለም አቀፍ ተቀባይነት ያገኘና በዝርዝር ኦዲት ተደርጎ ከሚገኘው ጥቅም ያላነሰ ውጤት ሊያስገኝ የሚችል ዘመናዊ፣ በተመጣጣኝ የሰው ሀይል እና ወጭ ስራውን ለማከናወን ጊዜና ገንዘብ ቆጣቢ በመሆኑ የተመረጠ ዘዴ እና በሃብት አስተዳደርና አጠቃቀም ዙሪያ ስጋት ያለበትን አካባቢ ትኩረት ስለሚሰጥ አዋጭ በመሆኑ ነው፡፡

የንሞና ኦዲት ስልትን አስመልክቶ ካለፈዉ በጀት ዓመት አፈፃፀም የዕቅድ ክንውን በንጽጽር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ-3 የኦዲት ስልት፤

ተ.ቁ	የኦዲት ስልት	2012ሂሣብ		2013 ሂሣብ	
		ክንውን ብዛት	%	ክንውን	%
1	ንሞና	227	75.42	100	72
2	ልዩ ኦዲት	74	24.58	38	28
	ድምር	301	100	138	100

በንሞና የኦዲት ዘዴ ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች የ2013 ክንውን 100(72%) ከ2012 ክንውን 227 (75.42%) ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት 127(55.95%) የቀነሰ ሲሆን የ2013 የልዩ ኦዲት ክንውን 38(28%) ከ2012 ክንውን 74(24.58%) ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት 36(48.65%) የቀነሰ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በክልሉ ባጋጠመው የፀጥታ ችግር ምክንያት አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በመታወጁ የኦዲት ስራ ባለመከናወኑ ነው፡፡

1.3. የኦዲት አስተያየቶች፣

የ2013 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ተደርጎ ወጪ የሆኑ ሪፖርቶች 138 ሲሆኑ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት ከ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ጋር ተነፃፅሮ እንደሚከተለው ከዚህ ቀጥሎ ተመልክቷል፡፡

ሠንጠረዥ-4 የኦዲት አስተያየቶች፣

ተ.ቀ	የኦዲት አስተያየት	2012 ሂሣብ		2013 ሂሣብ	
		የመ/ቤት ብዛት	በ%	የመ/ቤት ብዛት	በ%
1.	አስተያየት መስጠት አለመቻል	-----		1	1
2.	አጥጋቢ አይደለም	25	8	6	4
3.	ከዚህ በስተቀር	157	52	59	43
4.	ንፁህ	36	12	27	20
5.	አስተያየት ያልተሰጠው	9	3	7	4
6.	ልዩ ኦዲት	74	25	38	28
	ድምር	301	100	138	100

ከሰንጠረዡ እንደምንረዳው የ2013 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ 138 መ/ቤቶች ውስጥ ለ59 (43%) ከዚህ በስተቀር ፣ ለ6(4%) አጥጋቢ አይደለም፤ለ27(20%) ንፁህ አስተያየት፣ 7(4%) መ/ቤቶች የመጀመሪያ ኢንትሪም ሂሳብ ኦዲት ስራ ብቻ የተጠናቀቀ በመሆኑ አስተያየት ያልተሰጣቸው እና 38(28%) መ/ቤቶች የልዩ ኦዲት ስራ በመሆናቸው የኦዲት አስተያየት መስጠት የማይጠበቅባቸው ናቸው፡፡

በ2012 በጀት ዓመት ኦዲት ተደረጎ የተሰጠዉ የኦዲት አስተያየት በ2013 በጀት ዓመት ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር ሲነጻጸር " **ንፁህ አስተያየት የሚለው"** ከ36 ወደ 27 መ/ቤት (በ25%) የቀነሰ ቢሆንም አሁንም በአንዳንድ መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ እና የሀብት አስተዳደር ስርዓቱ አለመሻሻሉን ያሳያል፤**"አስተያየት መስጠት አለመቻል" ወደ 1-መ/ቤት** (በ100%) የጨመረ መሆኑ የኦዲት ማስረጃዎች አቅርቦት ገደብ መታየቱን የሚያመላክት ሲሆን በሌላ በኩል " **አጥጋሚ አይደለም**

የሚለው" ከ25 ወደ 6 መ/ቤት (በ76%) የቀነሰ ቢሆንም አሁንም በሀብት አስተዳደር ስርዓቱ እና በሪፖርት አቀራረብ ላይ ያሉ ጉልህ መዛባቶች እየተስተካከሉ አለመሆኑን ያመላክታል፡፡ የሂሳብ አሰራሩ የኦዲት አስተያየት የማይሰጥበት የልዩ ኦዲት ሂሣብ ደግሞ ከ74 ወደ 38 መ/ቤት (በ48.64%) መቀነሱ ሲታይ በክልሉ ባጋጠመው የፀጥታ ችግር ምክንያት የቀረቡትን የልዩ ኦዲት ስራዎች ሙሉ በሙሉ ማጠቃለል ባለመቻሉ የመጣ ልዩነት መሆኑን ያመላክታል፡፡

የኦዲት አስተያየት መገለጫዎች፤

1. "**አጥጋቢ አስተያየት**"የሚሰጠው ጉልህና መሰረታዊ የሚባል ግኝትና የአሰራር ችግር ያልተገኘባቸው መ/ቤቶች ናቸው፡፡
2. "**ከዚህ በስተቀር**" የሚለው አስተያየት የተሰጠባቸው የኦዲት ሪፖርቶች ከተወሰኑ ጉልህ ነገር ግን መሰረታዊ ያልሆኑ ግኝቶችና የአሰራር ችግሮች በስተቀር የተሻለ አፈፃፀም የሚታይባቸው ናቸው፡፡
3. **"አጥጋቢ አይደለም"** የሚለው አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶች መንግስት የመደበላቸውን ሀብት /ገንዘብ/ በአግባቡና ህጉ በሚፈቅደው አሰራር መሠረት ስራ ላይ ያላዋሉ፤የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመባቸው፤ጉልህና መሠረታዊ ግኝቶችና የአሰራር ችግሮች የተስተዋሉባቸው ናቸው፡፡
4. **"አስተያየት መስጠት አልተቻለም"** የሚለው አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶች ደግሞ መንግስት የመደበላቸውን ሀብት እንዴት ስራ ላይ እንዳዋሉት የሚገልጽ ማስረጃ ያልቀረበላቸው፣የውስጥ ቁጥጥር ስርዓታቸው በጣም የተዳከመ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት በኦዲት ለማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በተራ ቁጥር 3 እና 4 የተገለጹት አስተያየቶች የሚሰጧቸው መ/ቤቶች ግኝቶቻቸውና የአሰራር ችግሮቻቸው ጉልህና መሰረታዊ የሆነባቸው መ/ቤቶች ናቸው፡፡ ስለሆነም የሚመለከታቸው ሁሉ በሪፖርቶቹ የቀረቡ ችግሮች ጉልህና መሰረታዊ መሆናቸውን በመገንዘብ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ይጠበቅባቸዋል፡፡

1.3.1. **"አጥጋቢ አይደለም"** የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት መ/ቤት፤

የ2013 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረገት 138 መ/ቤቶች ውስጥ 6(4%) መ/ቤት የሂሳብ አያያዝና የገንዘብ አስተዳደሩ እንዲሁም የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ አጥጋቢ ሆኖ ባለመገኘቱ ይህም ጉልህና መሰረታዊ ችግር በመሆኑ **"አጥጋቢ አይደለም"** የሚል የኦዲት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ይህ የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት መ/ቤት እና ለአስተያዩቱ መነሻ ምክንያቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1.3.1.1. **ሞረትና ጅሩ ወረዳ ገቢዎች**

- በማነስ የተሰበሰበ ከመቀጠር የሚገኝ ስራ ግብር ገቢ ብር 40,014.43፣
- በግብር ውሳኔ መሰረት ያልተሰበሰበ ግብርና ታክስ ብር 2030.00፣
- ተወስኖ ያልተሰበሰበ አስተዳዳራዊ ቅጣት ብር 20,000.00፣

- በውዝፍ የሚገኝ ግብር፣ታክስ፣ወለድ እና አስተዳደራዊ ቅጣት ብር 197,989.34፣
- የገጠር መሬት መጠቀሚያና የእርሻ ስራ ገቢ ግብርን ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣
- ሂሳባቸውን በታክስ ኦዲተር ያላስመረመሩ 7-ደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ ነጋዴዎችን ሂሳብ ኦዲት አድርጎ አስተያየት መስጠት አለመቻሉ፣
- የካፒታል ዋጋ እድገት ገቢ ግብር ሂሳብን ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣
- የወጪ መጋራት ገቢ ሂሳብን ኦዲት ማድረግ አለማቻሉ፣

1.3.1.2. አንኮበር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

- የጥሬ ገንዘብ ሂሳብን ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣
- ለኦዲት ያልቀረቡ የመደበኛና የእንስሳት ጤና ገቢ ሂሳብ ብር 46,782.00፣
- ኦዲት ማድረግ ያልተቻለ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 6,087,421.61፣
- አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 39,599.00፣
- ባልተሟላ ማስረጃ የፀደቀ የወጪ ሂሳብ ብር 46,543.40፣
- የስራ ዝርዝር ወረቀት ሳይቀርብለት የተከፈለ የግንባታ ክፍያ ብር 230,616.68፣
- በብልጫ የፀደቀ የወጭ ሂሳብ ብር 8,082.07፣
- ከግዥ ስርዓት ውጭ ተፈፀመ ግዥ ብር 410,645.46፣
- ኦዲት ማድረግ ያልተቻለ የተከፋይ ሂሳብ ብር 10,121,942.41፣

1.3.1.3. ሲያ ደብርና ዋዩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

- ያልተሰበሰበ ከመቀጠር የሚገኝ የስራ ግብር ገቢ ብር 93,979.30፣
- ከሽልማት ክፍያ ላይ መሰብሰብ ሲገባው ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ብር 4,899.95፣
- በውሉ መሰረት የዕቃ አቅርቦት ለዘገየበት ያልተሰበሰበ መቀጫ ብር 8,666.87፣
- ለኦዲት ያልቀረቡ የመደበኛ እና የስፖርት ምክር ቤት የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ብር 23,776.10፣
- የእድሜ ትንተና ያልተዘጋጀለት በመሆኑ ኦዲት ማድረግ ያልተቻለ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 34,224733.78፣
- የተፈጥሮ ሚዛኑን ያልጠበቀ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 552,133.40፣
- ከ3ኛ ወገን ማረጋገጫ ያልቀረበለት የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 11,313,702.05፣
- ከግዥ በፊት የንብረት ገቢ ደሰኝ /ሞዴል19/ የተቆረጠለት ግዥ ብር 117,089.10፣
- አላግባብ የተከፈለ የወሎ አበል እና የነዳጅ ክፍያ ብር 23,413.25፣
- ደረሰኝ ሳይቀርብለት የተፈፀመ ክፍያ ብር 24,170.00፣
- የእድሜ ትንተና ያልተዘጋጀ በመሆኑ ኦዲት ማድረግ ያልተቻለ የተከፋይ ሂሳብ ብር 14,238,873.52፣

1.3.1.4. ማቻከል ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት

- ኦዲት አድርጎ አስተያየት መስጠት ያልተቻለ የመደበኛ ገቢ ሂሳብ ብር 12,385,278.62፣
- ኦዲት አድርጎ አስተያየት መስጠት ያልተቻለ የገጠር መሬት መጠቀሚያና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር ብር 204,180.00፣
- የወጭ መጋራት ሂሳብን ኦዲት አድርጎ አስተያየት መስጠት አለመቻሉ፣
- በግብር ስሌት መሰረት ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ገቢ ሂሳብ ብር 16,235.00፣
- ተወስኖ ያልተሰበሰበ ተርንኦቨር ታክስ ብር 3,820.00፣
- በወቅቱ ይልተሰበሰበ ውዝፍ ግብርና ታክስ ብር 77,435.80፣

1.3.1.5. ደንበጫ ከተማ አስተዳደር ገንዘብ ጽ/ቤት

- በጥሬ ገንዘብ ሌጀር እና በቆጠራ መካከል የታየ ልዩነት ቆጠራ በማነስ ብር 2,733.97፣
- ለመደበኛ፣ለመናኸሪያ፣ለስፖርት ምክር ቤት እና ለፒኤፍኤም ሂሳቦች የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ያልተዘጋጀ መሆኑ፣
- በባንክ ሌጀር እና በባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ መካከል የሚታይ ልዩነት ብር 22,110.33፣
- በወቅቱ ያልተሰበሰበ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 2,239,540.07፣
- በወቅቱ ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ ብር 1,747,281.68፣
- ለመናኸሪያ ሂሳብ ወርሃዊ ሪፖርት የማይዘጋጅ መሆኑ፣
- የተፈጥሮ ሚዛኑን ያልጠበቀ የተጣራ ሃብት ሂሳብ ብር 342,595.57፣

1.3.1.6. ወግዲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

- በጥሬ ገንዘብ ሌጀር እና በቆጠራ መካከል የታየ ልዩነት ቆጠራ በማነስ ብር 1,419,541.76፣
- በባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ እና በባንክ ሂሳብ ሌጀር መካከል የታየ ልዩነት ሪፖርት በመብለጥ ብር 335,612.92፣
- የመናህሪያ እና የስፖርት ምክር ቤት ሂሳብን ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣
- የእድሜ ትንተና ያልተዘጋጀ በመሆኑ የተሰብሳቢ ሂሳብን ኦዲት ማድረግ ያልተቻለ ብር 32,918,595.65፣
- በወቅቱ ያልተወራረደ/ያልተሰበሰበ ሂሳብ ብር 20,000.00
- ከግዥ ስርዓት ውጭ የተፈፀመ ግዥ ብር 169,800.00፣
- በብልጫ የተከፈለ የወጭ ሂሳ ብር 45,537.20፣
- የክፍያ ምስክር ወረቀት ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 11,250.00፣
- የእድሜ ትንተና ያልተዘጋጀ በመሆኑ የተከፋይ ሂሳብን ኦዲት ማድረግ ያልተቻል ሂሳብ ብር 16,245,186.72፣

1.3.2. **"አስተያየት መስጠት አልተቻለም"** የሚለው የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው

የ2013 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉት 138 መ/ቤቶች ውስጥ 1(1%) መ/ቤት መንግስት የመደበውን ሀብት እንዴት ስራ ላይ እንዳዋለው የሚገልጽ ማስረጃ ያላቀረበ፣የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቱ በጣም የተዳከመ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት በኦዲት ለማረጋገጥ ያልተቻለበት ነው፡፡

1.3.2.1. ስማዳ ወረዳ ነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጭ ማዕከል

- የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣
- የዕድሜ ትንተና ያልተዘጋጀ በመሆኑ ኦዲት ማድረግ ያልተቻለ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 29,277,938.76፣
- በወቅቱ ያልተሰበሰበ /ያልተወራረደ/የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 1,546,565.38፣
- ተቀፅላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 24,395,178.25፣
- ከ3ኛ ወገን ማረጋገጫ ያለቀበለት ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 2,345,114.15፣
- ከግዥ ስርዓት ውጪ የተፈፀመ ክፍያ ብር 775,767.53፣
- ባልተሟላ ማስረጃ በወጪ የፀደቀ ሂሳብ ብር 784,632.81፣
- አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 377,754.30፣
- ደረሰኝ /ፋክቱር/ ሳይቀርብለት የተፈፀመ የግንባታ ክፍያ ሂሳብ ብር 11,696.00፣
- ኖርማላይዜሽን ስርዓቱን ተከትሎ ነዳጅ የማይሞላ በመሆኑ የነዳጅ ሂሳብ ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣
- የግንባታ የስራ ዝርዝር ሳይቀርብለት የተፈፀመ ክፍያ ብር 116,600.33፣
- የእድሜ ትንተና ያለተዘጋጀ በመሆኑ ኦዲት ማድረግ ያልተቻለ የተከፋይ ሂሳብ ብር 10,726,586.76፣
- በወቅቱ ያልተከፈለ /ያልተወገደ/ ተከፋይ ሂሳብ ብር 319,657.25፣
- ተቀፅላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት የተከፋይ ሂሳብ ብር 644,811.83፣

1.4. **መልስ ያልሰጡ መ/ቤቶች፣**

ይህ ሪፖርት እስከተጠቃለለበት ሰኔ 24/2014 ዓ/ም ድረስ መልስ ያልሰጡ መ/ቤቶች ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ክልል ማዕከል መ/ቤቶች

1. አብክመ ፖሊስ ኮሚሽን
2. ሴቶችና ህፃናት ቢሮ
3. አብክመ ግብርና ምርመር ኢንስቲቲዩት
4. ጎንደር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት
5. በጌምድር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ
6. ደጀን ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ

ምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳደር

7. ደንበጫ ወረዳ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ
8. ብቸና ከተማ ጤና አጠባበቅ ጠቢያ

9. ቢቡኝ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት

10.ጎንቻ ሲሶ ገቢዎች ጽ/ቤት

11.ብቸና ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት

12.አነደድ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት

13.እነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት

14.ማቻከል ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት

15.ባሶ ሊበን ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት

ማዕከላዊ ጎንደር ዞን አስተዳደር

16.ጎንደር ከተማ አሰ/ገቢዎች ጽ/ቤት

ሰሜን ጎንደር ዞን አስተዳደር

17.ዳባት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማእከል

ደቡብ ጎንደር ዞን አስተዳደር

18.ስማዳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ

19.ሊቦ ከምከም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማእከል

20.ደብረ ታቦር ከተማ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ

21.ስማዳ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት

አዊ ብሄረሰብ አስተዳደር

22.ዳንግላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ

ደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር

23.መቅደላ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት

24.ወግዲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር

25.ሞረትና ጅሩ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት

26.ሞረትና ጅሩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

27.አንኮበር ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት

28.አንኮበር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ

29.ሲያ ደብርና ዋዩ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ

30.ሲያ ደብርና ዋዩ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት

በአጠቃላይ መልስ አሰጣጡ ባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ጊዜ በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉ 227 መ/ቤቶች መልስ ያልሰጡት 74(32.60%) ጋር ሲነጻጸር በበጀት ዓመቱ በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉት 100 መ/ቤቶች መልስ ያልሰጡት 30(30%) ስለሆኑ የዚህ ዓመት መልስ አሰጣጥ ካለፈዉ በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር እየጨመረ የመጣ ቢሆንም አሁንም የፋይናንስ ግልጽ አሰራርና ተጠያቂነት ሥርዓት ከማጠናከር አኳያ ድክመቶች እንዳሉ የሚያመላክት እና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ በኩል እጥረቶች እንዳሉባቸው ያሳያል፡፡ በልዩ ኦዲት ከተሰሩት 38 መ/ቤቶች ውስጥ ደግሞ እርምጃ ያልተወሰደባቸው 38(100%) በመሆናቸው እርምጃ የመውሰድ ሂደቱ አዝጋሚ ሆኖ ይታያል፡፡

1.5 የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ውጤት፤

1.5.1. የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ጉድለት፣

ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በየጊዜው ቁጥጥር እያደረጉ መያዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዋና ኦዲተር መ/ቤት በኩል የበጀት ዓመቱን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ የማረጋገጥ ስራ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ ያለ ተግባር ነው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የኦዲት ሥራዎች ላይ ሁኔታዎች ትኩረት ሲሰቡና የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንዲረጋገጥ በልዩ ሁኔታ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በወቅቱ በመቀበል የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ የማመዛዘን ተግባር የሚከናወን ሲሆን የኦዲት ውጤቱ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ-5 **የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣**

ተ.ቁ	ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች	ጉድለት				የገንዘብ ያዥ ብልጫ	የሌጀር ከወጪ ቀሪ ከቆጠራ ልዩነት			
		የ መ/ቤት ብዛት	ከአሁን ገንዘብ ያዥ	ከቀድሞ ገንዘብ ያዥ	ድምር		የ ማቤት ብዛ ት	በመብለጥ	የ ማቤ ት ብዛ ት	በማነ ስ
1.	ክልል/ማዕከል	4	45,755.96	746,522.87	792,278.83		2	633,215.79		
2.	ባህር ዳር ከተማ	1		34,873.94	34,873.94					
3.	ምዕ/ጎጃም									
4.	ምስራቅ ጎጃም	1		49,930.24	49,930.24					
5.	ማዕከላዊ ጎንደር									
6.	ሰሜን ጎንደር	1		99,011.71	99,011.71					
7.	ምዕራብ ጎንደር						1	249,026.30		
8.	ደቡብ ጎንደር	2		197,963.41	197,963.41					
9.	የአዊ ብሔ/አስተ/									
10.	ሰሜን ወሎ									
11.	ደቡብ ወሎ	3		1,045,014.45	1,045,014.45					
12.	ሰሜን ሸዋ	1		56,643.52	56,643.52					
13.	ኦሮሞ ብሔ/አስተ/									
14	ዋግኽምራ									
ድምር		**13**	45,755.96	**2,229,960.14**	**2,275,716.10**		**3**	**882,242.09**		

የ2013 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች በድምሩ ብር 2,275,716.10 ጉድለት የተገኘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 2,229,960.14 ከቀድሞ ገንዘብ ያዦች የተገኘ ጉድለት ነው፡፡

እንዲሁም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ (ሰኔ/30) በጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ መከታተያ ሌጀር መሠረት መገኘት ያለበት እና በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሲነጻጸር በ3 መ/ቤቶች ብር 882,242.09 የተቆጠረ ገንዘብ ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በማነስ ተስተውሏል፡፡ ዝርዝሩን (አባሪ 2 ይመልከቱ፡፡)

የጥሬ ገንዘብ ጉድለት የታየባቸው መ/ቤቶች፡-

- አብርሀ ጅራ የመጀመያ ደ/ሆስፒታል የግዥ ባለሙያ ከ01/10/2009-30/7/2013 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን በጉድለት የተገኘ ጥሬ ገንዘብ ብር 525,669.84 እና የግዥ ባለሙያ የሰበሰቡት እና ፈሰስ ያደረጉት የቅድመ ግብር ሂሰብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 17,247.66 በድምሩ ብር 542,917.50፣
- ተንታ ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ረዳት ገንዘብ ያዥ የነበሩት ከ01/11/2011-3/01/2013 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 130,562.63፣
- ጃቢ ጠህናን ወረዳ ፍ/ቤት ዋና ገ/ያዥ ከ/14/06/09 እስከ 11/03/2010 እና ከ29/09/2010 እስከ 24/05/2014 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 129,826.54፣
- የስማዳ ወረዳ የየኳሳ 1ኛ ደ/ት/ቤት ገንዘብ ያዥ የነበሩት ከ12/7/2006-20/4/2010 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ ጉድለት ብር 117,074.69፣
- በየዳ ወረዳ ውሃ መስኖና ኢነርጅ ልማት ጽ/ቤት ገንዘብ ያዥ የነበሩት ከ19/01/2010-03/6/2013 ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 19,771.72 እና በግዥ ኦፊሰር በነጠላ ሰነድ ወጭ የተደረገ እና ፈሰስ የተደረገው ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 79,240.00 በድምሩ ብር 99,011.72፣
- ከለላ ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ረዳት ገ/ያዥ የሆኑት ስራ ከጀመሩበት ከ01/11/2007 እስከ 7/2/2010 ዓም ድረስ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 901,919.04፣
- የአምቦ ሜዳ ንዑስ ማዘጋጃ ቤት የዕለት ገንዘብ ሰብሳቢ የነበሩት ከ03/8/2003-27/10/2009 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 80,888.72፣
- አብርሀ ጅራ አጠ/2ኛ/ደ/ት/ቤት ገንዘብ ያዥ ከ01/07/2006 እስከ 01/08/2013 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን በጉድለት የተገኘ ጥሬ ገንዘብ 73,778.83፣
- በእንሳሮ ወረዳ ልጅ ስዩም ገ/ህይወት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ገንዘብ ያዥ የነበሩት ከ15/08/2005--30/01/2007 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 56,643.52፣
- ባሶ ሊበን ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ዋና ገንዘብ ያዥ የነበሩት ከ02/10/2006-07/10/2008 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 49,930.24፣
- የአማራ ህዝብ ዝክረ ታሪክ ማዕከል ዋና ገንዘብ ያዥ ከ21/9/2011-3/12/2013 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 45,755.96፣
- የጣና ክፍለ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ዋና ገንዘብ ያዥ የነበሩት ከ01/11/2008-30/5/2010 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 34,873.94፣
- ውጫሌ ከተማ መሪ መዘጋጃ ቤት ዋና ገንዘብ ያዥ ከ17/5/2010-25/10/2010 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 12,532.78፣ናቸው፡፡

ከጥሬ ገንዘብ ጉድለት ጋር በተያያዘ ለግኝቶች በዋና ምክንያትነት የሚጠቀሱት፤

- በየጊዜው የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ በማድረግ ከተያዘው የሌጀር ከወጪ ቀሪ ሚዛን ጋር እንዲመሳከር አለማድረግ፣
- የተቋማት የሂሳብ አያያዝ እና የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማ መሆኑ፣
- ገንዘብ ያዦች የስራ ለውጥ በሚያደርጉበት ጊዜ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ በውስጥ ኦዲተር እየተመረመረ ርክክብ የማይደረግ መሆኑ፣
- በረዳት ገንዘብ ሰብሳቢዎች የሚሰበሰበው ገንዘብ በየእለቱ ለዋና ገንዘብ ያዦች ፈሰስ አለማድረግ፣
- የግዥ ሰራተኞች በተሰብሳቢ ሂሳብ የወሰዱትን ገንዘብ በወቅቱ ሳያወራርዱ በድጋሜ ጥሬ ገንዘብ የሚሰጥ በመሆኑ በቆይታ ብዛት የጥሬ ገንዘብ ብክነት የሚከሰት መሆኑ፣

1.5.2. የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ማድረግ ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች፣

የ2013 በጀት ዓመት ሂሣባቸው በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉት 100 መ/ቤቶች ውስጥ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ለማድረግ ያልተቻለባቸው 7(7%) መ/ቤቶች ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ክልል ማዕከል መ/ቤቶች

1. ባህር ዳር አካል ጉዳተኞች ተሃድሶ ማዕከል

ማዕከላዊ ጎንደር ዞን አስተዳደር

2. ጎንደር ጤና አጠባበቅ ጣቢያ

ደቡብ ጎንደር ዞን አስተዳደር

3. ስማዳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማ

አዊ ብሄረሰብ ዞን አስተዳደር

4. ዚገም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማ
5. ዳንግላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማ
6. አዩ ጓጉሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማ-2010

ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር

7. አንኮበር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማ

ከላይ በተዘረዘሩት 7 መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2013 ዓ.ም ላይ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሲሆን ለዚህም ዝርዝር ምክንያቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡-

- በጥሬ ገንዘብ መቆጣጠሪያ ሌጆሮች እና የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ላይ ለቆጠራ የተደረሰበት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በውስጥ ኦዲተሮች ምልክት ባለመደረጉ፣
- ሰኔ 30/2013 ዓ/ም የተራድኦ ሂሳቦች በሙሉ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የማይደረግ በመሆኑ፣

- የተሟላ የሂሳብ መዝገብ /ሌጀር/ ተዘጋጅቶ የሂሳብ ምዝገባ ያልተደረገና ትክክለኛውን ከወጪ ቀሪ ሊያመላክት ባለመቻሉ፣
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በካዝና የሚገኝ ጥሬ ገንዘብ እና እንደጥሬ ገንዘብ የሚቆጠሩ ሂሳቦች የተሟላና ህጋዊ ቆጠራ ባለመደረጉ፣
- ገንዘቡ በአንድ ገንዘብ ያዥ ተይዞ እየተዳደረ ባለበት ሁኔታ የተለያዩ የተራድኦ ሂሳቦችን ሳይጨምር የመደበኛ ሂሳብ ጥሬ ገንዘብ ብቻ ነጥሎ ቆጠራ የሚደረግ በመሆኑ፤
- ለረጅም ዓመታት እየተንከባለለ የመጣ የጥሬ ገንዘብ መቆጣጠሪያ ሌጀር እና የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ልዩነት የፈጠረ ቢሆንም በኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች አማካኝነት መንስኤው ተለይቶ የማስተካከያ እርምጃ የማይወሰድ መሆኑ፣

ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ስለሆነ መ/ቤቶቹ አሰራራቸውን እንዲያስተካክሉና በየጊዜውም በውስጥ ኦዲተሮቻቸው እየተከታተሉ የጥሬ ገንዘብ አስተዳደራቸውን እንዲያሻሽሉ በየሪፖርቱ አሳስበናል፡፡

1.6. የገቢ ሂሳብ ኦዲት ውጤት

1.6.1. የማጭበርበር ወንጀል የተፈፀመበት *የገቢ ሂሳብ እና ዘዴዎች፣*

በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ2 መ/ቤቶች ብር 44,307.00 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡ማጭበርበሩ የተፈጸመባቸው መ/ቤቶችና ዘዴዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- የጣና ክፍለ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ብር 34,307.00 የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ጥራዝ ቅጠሎች ተነቅለው እንዲጠፉ በማድረግ እንዲሁም በኦርጅናል የገቢ ደረሰኝ ቅጠል የተሰበሰበውን የገንዘብ መጠን በካርበን ኮፒው ሳያስቀምጡ ሌሎች ግለሰቦች የከፈሉት ገንዘብ በካርበን ኮፒው ደረሰኝ ቅጠል ላይ በማስፈር በኦርጅናል ደረሰኝ ቅጠል የተሰበበው ገንዘብ ለግል ጥቅም ማዋል፣
- ጃቢ ጠህናን ወረዳ ፍ/ቤት ብር 10,000.00 ከንብረት ክፍል ወጭ ሳይደረግ እና በደረሰኝ ቅጠሎች ተሰብስቦ ለግል ጥቅም የዋለ የገቢ ሂሳብ፣

በመሆኑም ድርጊቱን ከፈጸሙት አካላት የሚፈለገው የህዝብ ሀብት ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ብናሳስብም እስከ ሰኔ 24/2014 ዓ.ም ድረስ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አልተገለፀልንም፡፡

1.6.2. ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ተሰብስቦ ለግል ጥቅም የዋለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 7,598,879.50

የተጨማሪ እሴት ታክስን አስመልክቶ በወጡ ደንብና መመሪያዎች መሠረት ማንኛውም በተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ደረጃ የሚገኝ ድርጅት በከፋይነት ተመዝግቦ እቃ/አገልግሎት ሲያቀርብ ለክፍያው የቫት ደረሰኝ/ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ ያለበት እና ግዥ የሚፈጽሙ አካላትም ማስረጃው እንዲቀርብላቸው የማድረግ ሃላፊነት የተጣለባቸው ቢሆንም በ1 መ/ቤት ብር 7,598,879.50 የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳይቀርብለት ክፍያ ተፈጽሞ የተጨማሪ እሴት ታክሱ ለመንግስት ገቢ ሳይሆን ተገኝቷል፡፡ የተጨማሪ እሴት ታክሱ ለመንግስት ገቢ ሳይደረግ ክፍያ የተፈፀመበት መ/ቤት፡-

- **አብክመ ገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ ብር 7,598,879.50** ከአደም ኢንጅነሪንግና ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሁለት ሮሎዎች ተገዝተው ክፍያ ሲፈፀም ህጋዊ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳይቀርብ በመፈፀሙ ለመንግስት ገቢ ያልሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣

በመሆኑም ታክሱ ከመንግስት ተቋማት ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ተሰብስቦ ለግል ጥቅም የዋለ በመሆኑ አቅራቢው ታክሱን ለገቢ ሰብሳቢው አካል ገቢ አድርጎ ማስረጃ እንዲያቀርብ መደረግ እንዳለበት እያስገነዘብን ታክሱን ለመመለስ ፈቃደኛ ካልሆነ በሚመለከተው የፍትህ አካል ክስ በመመስረት ከተጠቃሚው የተሰበሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስ ወደ መንግስት ካዝና ገቢ የሚሆንበት ሁኔታ እንዲመቻች በሪፖርታችን ብናሳስብም የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ምላሽ አልደረሰንም፡፡

1.6.3. ያልተሰበሰበ (በውዝፍ) የሚገኝ ገቢ፤

የ2013 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ 138 መ/ቤቶች ውስጥ በ29 መ/ቤቶች ብር 569,589,919.15 ሥራ ላይ ባለው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት ገቢው በ□ቅቱ ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ □ር□ሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ-6 በውዝፍ የሚገኝ ገቢ፣

ተ.ቁ	ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት	የ2012 በውዝፍ የሚገኝ/ያልተሰበሰበ ገቢና ቅጣት ሂሣብ			የ2013 በውዝፍ የሚገኝ /ያልተሰበሰበ ገቢና ቅጣት ሂሣብ		
		የመ/ቤት ብዛት	የገንዘቡ ልክ	%	የመ/ቤት ብዛት	የገንዘቡ ልክ	%
1	የክልል መ/ቤቶች	14	2,749,550.80	1	2	194,555.06	0.03
2	ባህር ዳር ከተማ	1	82,894,648.99	28	1	425,658,470.67	74.73
3	ምዕራብ ጎጃም	11	18,046,753.32	6	2	303,355.67	0.05
4	ምሥራቅ ጎጃም	4	42,135,574.18	14.5	9	19,144,716.37	3.36

5	ማዕከላዊ ጎንደር				1	118,203,059.47	20.75
6	ሰሜን ጎንደር	2	247,447.74	0.10	2	181,753.01	0.03
7	ምዕራብ ጎንደር				1	40,154.98	0.01
8	ደቡብ ጎንደር	5	18,520,319.99	6	3	856,921.27	0.15
9	አዊ ብሔረሰብ				1	46,826.16	0.01
10	ደቡብ ወሎ	21	41,419,625.10	14	1	1,865,830.66	0.34
11	ሰሜን ወሎ	17	50,220,859.25	17			
12	ሰሜን ሸዋ	24	37,803,166.89	13	6	3,094,275.83	0.54
13	ዋግ ኽምራ ብሔረሰብ	4	578,052.07	0.20			
14	ኦሮሞ ብሔረሰብ	4	567,362.14	0.20			
	ድምር	**107**	**295,183,360.47**	100	29	**569,589,919.15**	100

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው የ2013 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ 138 መ/ቤቶች ውስጥ በ29 መ/ቤቶች ብር 569,589,919.15 ባለው የገቢ አሰባሰብ ስርዓት መሰረት ገቢ በወቅቱ ሳይሰበሰብ በውዝፍነት ተገኝቷል፡፡ ከፍተኛ ያልተሰበሰበ የመንግስት ገንዘብ ከሚታይባቸው ዞኖች መካከል ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ብር 425,658,470.67 (74.73%)፣ማዕከላዊ ጎንደር ዞን አስተዳደር ብር 118,203,059.47(20.75%)፣ምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳዳር ብር 19,144,716.37 (3.36%)፣ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር ብር 3,094,275.83 (0.54%)እና ደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር ብር 1,865,830.66 (0.34%)፣ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ::

መንግስት የበጀት ዓመቱን ሥራ ለማከናወን ዕቅድ የሚነድፈው ገቢ የመሰብሰብ ስልጣን ከተሰጣቸው መ/ቤቶች ይሰበሰባል ተብሎ የታቀደውን በታሳቢነት በመያዝ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም ገቢን በወቅቱ መሰብሰብ ተገቢው ትኩረት ሊሰጥ እንደሚገባ ለየመ/ቤቶች በተላከው ሪፖርት ተገልጿል፡፡ ያልተሰበሰበ ገቢ ተብሎ ከተያዘው ገንዘብ ዉስጥ እስከዚህ ሪፖርት ጥንቅር ሰኔ 24/2014 ዓ/ም ድረስ ስለመሰብሰቡ ግብረ-መልስ አልተሰጠም፡፡ (ዝርዝሩን አባሪ 2 ይመልከቱ)፡፡

1.6.4. ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች፣

ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ተሟልተው እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ17 (17%) መ/ቤቶች ብር 703,529,247.33 የያዙ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

የገቢ ደረሰኞችን ለኦዲት ካላቀረቡት መ/ቤቶች መካከል ባህር ዳር ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 698,521,067.47 ያያዙ 1704.68 ጥራዝ የመደበኛ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ወንበርማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 2,836,506.70 የያዙ 53.11 ጥራዝ የስፖር ምክር ቤት፣84.46 ጥራዝ የእንስሳት ገቢ ሂሳብ መሰብሰቢያ፣54.39 ጥራዝ የመደበኛ ገቢ ሂሳብ መሰብሰቢያ እና 34.40 ጥራዝ የመናህሪያ የገቢ ሂሳብ መሰብሰቢያ፣169.38 ጥራዝ የወረዳው ገቢዎች ጽ/ቤት የገቢ ሂሳብ ማጠቃለያ ደረሰኞች፣ቢቡኝ ወረዳ ነ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 664,190.00 የያዙ የገጠር መሬት መጠቀሚያና የእርሻ ስራ ግብር መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣እብናት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 492,428.27 ያያዙ 417.64 ጥራዝ የስፖርት ምክር ቤት እና ጥራዝ 19 የእንስሳት ሀብት ልማት የገቢ ሂሳብ መሰብሰቢያ ደረሰኞች እና ጃቢ ጠህናን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 272,768.01 የያዙ 22.06 ጥራዝ የስፖርት ምክር ቤት እና 31.36 የእንስሳት ገቢ ሂሳብ ማጠቃለያ ደረሰኞች፣ከብር 250,000.00 በላይ የያዙ ደረሰኞች ለኦዲት ባለማቅረብ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡

ይህም ለኦዲት ስራ ባልቀረቡት ደረሰኞች ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ባለመረጋገጡ በጉዳዩ ላይ አስተያየት ለመስጠት ገደብ የተጣለበትና ማጭበርበር ተሰርቶባቸው ይሁን አይሁን ጥርጣሬን ያሳደረ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለኦዲት ሊቀርቡ ካልቻሉ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች የገቢው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥና ደረሰኞቹን በሰወሩ/ባላቀረቡ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በየሪፖርቶቹ ብናሳስብም የተወሰደው እርምጃ እስከዚህ ሪፖርት ጥንቅር ሰኔ 24/2014 ዓ/ም ድረስ ምላሹ አልተገለፀም፡፡

1.7. የተሰብሳቢ ሂሣብ ኦዲት ውጤት፤

1.7.1. በወቅቱ ያልተሰበሰበ (ያልተወገደ) ተሰብሳቢ ሂሣብ፤

የ2013 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ48 መ/ቤቶች ብር 2,320,625,230.63 በወቅቱ በፋይናንስ የአሠራር ስርዓት መሠረት ሣይሰበሰብ (ሳይወገድ) ተገኝቷል፡፡ (ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል)፤

ሠንጠረዥ-7 በወቅቱ ያልተሰበሰበ /ያልተወገደ/ ሂሣብ፤

ተ.ቁ	ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት	2012 ሂሣብ			2013 ሂሣብ		
		የመ/ቤት ብዛት	የገንዘቡ ልክ	%	የመ/ቤት ብዛት	የገንዘቡ ልክ	%
1.	የክልል መ/ቤቶች	33	2,867,424,609.72	73	13	1,449,573,661.94	62.46
2	ባህር ዳር ከተማ	1	64,148,157.52	2	1	39,434,348.30	1.70
3	ምዕ/ጎጃም	9	143,135,279.15	4	7	108,181,620.60	4.66
4	ምስ/ጎጃም	8	73,939,236.66	2	6	383,984,879.64	16.55
5	ማዕከላዊ ጎንደር	2	38,381,207.32	1	1	47,746,727.52	2.05
6	ሰሜን ጎንደር	2	10,301,222.48	0.3	2	40,078,669.98	1.73
7	ምዕራብ ጎንደር	1	2,027,991.02	0.10	1	7,402,676.62	0.32
8	ደቡብ ጎንደር	6	60,468,228.84	2	7	115,645,152.43	5
9	አዊ ብሔረሰብ	6	56,856,960.68	0.1	8	110,666,990.71	4.76
10	ሰሜን ወሎ	13	204,651,406.63	5			
11	ደቡብ ወሎ	12	213,573,731.65	5			
12	ሰሜን ሸዋ	15	138,144,831.29	3.5	2	17,910,502.89	0.77
13	ኦሮሞ ብሄረሰብ	5	33,749,134.13	1			
14	ዋግኽምራ ብሔረሰብ	2	32,947,125.63	1			
ድምር		115	3,939,749,122.20	100	48	2,320,625,230.63	100

በአጠቃላይ በወቅቱ ያልተሰበሰበ /ያልተወገደ/ ተሰብሳቢ ሂሳብ ካለፈው ዓመት ብር 3,939,749,122.20 ጋር ሲነፃፀር በ2013 በጀት ዓመት ሂሣብ ላይ የተገኘው በመ/ቤቶች ቁጥር በ67 እና በገንዘብ መጠን በብር 1,619,123,891.57 ቀንሶ ተገኝቷል፡፡ ይህም በወቅቱ ያልተሰበሰበ /ያልተወገደ/ ተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የቀነሰ መሆኑን ያመላክታል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት የአስተዳደር እርከኖች ውስጥ በወቅቱ ያልተሰበሰበ /ያልተወገደ/ ከፍተኛ ተሰብሣቢ ሂሣብ ከሚታይባቸው መ/ቤቶች መካከል ጤና ጥበቃ ቢሮ ብር 758,971,347.99፣መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ ብር 287,049,901.89፣ደብረ ማርቆስ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 267,504,953.44፣ አብክመ ፖሊስ ኮሚሽን ብር 176,941,971.50፣አብክመ ስራና ስልጠና ቢሮ ብር 88,599,653.70፣አብክመ ገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ ብር 88,883,124.16፣ምስራቅ ጎጃም

ዞን ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማ ብር 68,684,718.95፣ዳንግላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማ ብር 47,876,219.61፣ጎንደር ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማ ብር 47,746,727.52፣ጃቢ ጠህናንወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 45,161,635.37፣ እብናት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 41,550,079.10፣ሊቦ ከምከም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ ማዕከል ብር 41,515,606.69፣ ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 39,434,348.30፣ቡሬ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 38,980,640.63 እና ዳባት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 38,464,916.8፣ከ30 ሚሊዩን በላይ የተሰብሳቢ ክምችት በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ ይሸፍናሉ፡፡

ተሰብሳቢ ሂሳቦች የራሳቸው የተወሰነ የመሰብሰቢያ ወይም ከመዝገብ የመሰረዣ ጊዜ እንዳላቸውና በመመሪያው መሠረት ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ በቁጥር 6/2004 በክፍል-4 በተላለፈው መመሪያ የተገለጸ ቢሆንም አንዳንድ መ/ቤቶች ተግባራዊ ባለማድረጋቸው ጊዜው በዘገየ ቁጥር ያለመሰብሰብ ዕድሉ እየሠፋ ስለሚሄድ መመሪያው በሚያዘው መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርቶቻችን ገልጸናል፡፡

ይህም ሂሳብ ትክክለኛ ተሰብሳቢና ባለቤት ያለው ስለመሆኑ በማረጋገጥ መ/ቤቶቹ ተሰብሳቢው ሂሳብ የተያዘበትን አግባብ በማጣራት በሚገኘው ውጤት መሠረት ተገቢውን እርምጃ እንዲወስዱ በሪፖርት ባሳሰብነው መሰረት ብር 6,344,668.22(0.27%) የተመለሰ ሲሆን ቀሪው ብር 2,314,280,562.41 ይህ ዘገባ ጥንቅር እስከተሰራበት ሰኔ 24/2014 ዓ.ም ድረስ ተሰብሳቢ ሂሳቡ ስላለበት ደረጃ አልተገለፀም፡፡

በሌላ በኩል የተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክለኛነት እንዳስፈላጊነቱ በሚመለከተው 3ኛ ወገን ማረጋገጫ እንዲቀርብለት የሚደረግ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ስለትክክለኛነቱ ከ3ኛ ወገን (ከሚሰበሰብባቸው አካላት) ለማረጋገጥ ከተጠየቁት የተሰብሳቢ ሂሳቦች መካከል በ6 መ/ቤቶች ብር 69,578,653.07 የ3ኛ ወገን ማረጋገጫ አልቀረበለትም፡፡ ከእነዚህ ተሰብሳቢ ሂሣቦች መካከል ሲያ ደብርና ዋዩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 11,313,702.05፣ስማዳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 2,345,114.15 እና አዲስ ዘመን ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,715,772.33፣ ከብር 1-ሚሊዮን በላይ የሦስተኛ ወገን ማረጋገጫ ያልተገኘላቸውን ተሰብሳቢዎች በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ፡

ይህም ሂሳብ ትክክለኛ ተሰብሳቢና ባለቤት ያለው ስለመሆኑ በማረጋገጥ መ/ቤቶቹ ተሰብሳቢው ሂሳብ የተያዘበትን አግባብ በማጣራት በሚገኘው ውጤት መሠረት ተገቢውን እርምጃ እንዲወስዱ በሪፖርት ያስገነዘብን ቢሆንም የተወሰደውን እርምጃ አስመልክቶ የተሰጠ ምላሽ የለም፡፡

1.7.2. በተቀጽላ ሌጀር ያልተመዘገበ ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

የ2013 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ7 መ/ቤቶች ብር 57,916,991.13 የመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመተላለፍ የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ተቀጽላ ሌጀር የተዘጋጀለት ተሰብሳቢ ሂሳብ ስለመኖሩ ይህ

ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 24/2014 ዓ.ም ድረስ የተሰጠ ግብረ መልስ ባለመቅረቡ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አልታወቀም፡፡

ሠንጠረዥ-8 በተቀጽላ ሌጀር ያልተመዘገበ ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

ተ.ቁ.	በክልል ማዕከላትና ዞን	የመ/ቤቱ ብዛት	የገንዘቡ ልክ	%
1	የክልል መ/ቤቶች	1	4,138,977.38	
2	ባህር ዳር ከተማ			
3	ምዕራብ ጎጃም	1	28,967,705.65	
4	ምስራቅ ጎጃም	1	78,696.79	
5	ማዕከላዊ ጎንደር			
6	ሰሜን ጎንደር			
7	ምዕራብ ጎንደር			
8	ደቡብ ጉንደር	2	24,674,055.55	
9	ሰሜን ወሎ			
10	ሰሜን ሸዋ			
11	ደቡብ ወሎ			
12	ኦሮምያ ብሔረሰብ ዞን			
13	አዊ ብሔረሰብ ዞን	2	57,555.76	
14	ዋግኽምራ			
	ደምር	7	57,916,991.13	

የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር አለመዘጋጀትን በተመለከተ አብክመ ፖሊስ ኮሚሽን ብር 4,138,977.38፣ ደንበጫ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 28,967,705.65፣ ስማዳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 24,395,178.25፣ ከብር 4 ሚሊዮን በላይ በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው ይገኛሉ፡፡

ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለትን ተሰብሳቢ ሂሣብ በተመለከተ ገንዘቡ ከማን እንደሚፈለግ ገላጭ ባለመሆኑና በጥቅሉ ስለተመዘገበ ባለቤቱን አውቆ ከሚመለከተው ላይ ለመሰብሰብ ወይም ከመዝገብ ለመሰረዝ የማያስችል በመሆኑ ተሰብሳቢ ሂሳቡ በየስሙ ተለይቶ የተቀፅላ ሌጀር ሊዘጋጅለትና ክትትል እየተደረገ ሊሰበሰብ/ከመዝገብ ሊሰረዝ/ እንደሚገባው በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡ (አባሪ 2 ይመልከቱ)፡፡

1.8. የወጪ ሒሣብ ኦዲት ውጤት፣

የ2013 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረገ መ/ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና የወጪ ሂሳብ ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1.8.1 የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት የወጪ ሂሳብ እና ዘዴዎች፣

በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መካከል በ7 መ/ቤቶች ብር 1,990,635.99 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡ ማጭበርበሩ የተፈጸመባቸው መ/ቤቶችና የአፈፃፀም ዘዴዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- የጃናሞራ ወረዳ የወይና ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት ብር 908,318.74 ላልተሰራ የካናል ግንባታ ስራ አላግባብ በብልጫ የተከፈለ ሂሳብ፣
- የመተማ ከተማ ሆስፒታል ብር 309,960.00 መስክ ሳይወጣ ቢሮ ውስጥ እያሉ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል እና ስልጠናው በተሰጠበት ከተማ ለመጡ የስልጠናው ተሳታፊዎች አላግባብ የተከፈለ የስልጠና አበል፣
- እብናት ወረዳ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል ብር 79,473.45 የወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት ሰራተኞች ከገጠር ቀበሌ እንደመጡ ተደርጎ በሚኖሩበት ከተማ ለተሰጠ ስልጠና አላግባብ የተከፈለ የስልጠና አበል፣የውሃ ማፋሰሻ ቦይ ሳይሰራ እደተሰራ ተደርጎ አላግባብ የተከፈለ ክፍያ፣ ከሚከፈላቸው የተጣራ ደመወዝ በላይ ተጨምሮ አላግባብ የተከፈለ ክፍያ እና በተሰብሳቢ ሂሳብ ተሰጥቶ ስራ ሳይሰራ አላግባብ ለግለሰብ ጥቅም የዋለ ሂሳብ፣
- ባህር ዳር ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 42,850.00 አላግባብ በድጋሜ፣በብልጫ የተከፈለ የውሎ አበል፣ የስልጠና እና የትራንስፖርት ክፍያ፣
- ሙሉ ዓለም የባህል ማዕከል ብር 16,983.54 መስክ ሳይወጣ ቢሮ ውስጥ እያሉ አለአግባብ የተከፈለ ውሎ አበል እና የትራንስፖርት ክፍያ፣
- አብክመ ቤቶች ልማት ድርጅት ብር 583,625.00 በባህር ዳር ከተማ ቀበሌ-15 ለተገነባው ህንፃ ስሚንቶ ግዥ ከጉና ትሬዲንግ ኃ/የተ/ማህበር ተፈጽሞ ለድርጅቱ ገቢ ያልተደረገ 1750 ኩንታል ስሚንቶ፣
- መካነ ሰላም ጠቅላላ ሆስፒታል ብር 49,425.26 አላግባብ በድጋሜ የተከፈለ ውሎ አበል እና ለኬዝ ቲም አስተባባሪዎች ከመመሪያ ውጪ የተፈፀመ ቶፕ አፕ ክፍያ፣

በመሆኑም ድርጊቱን ከፈጸሙት ኃላፊዎች እና ሰራተኞች የሚፈለገው የህዝብ ሀብት ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካከትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ለፍትህ አካላት ያሳወቅን ቢሆንም እስከ ሰኔ 24/2014 ዓ.ም በምን ደረጃ ላይ እንዳለ አልተገለፀልንም፡፡

1.8.2. አለአግባብ የተፈፀመ ክፍያ፣

ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈፀሙ ስለመሆናቸው ሲጣራ በ38(38%) መ/ቤቶች የተለያየ ዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈፀም በብልጫ እንዲሁም የመስክ ስራ ላላከናወኑ ሠራተኞች የተከፈለ የውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች በድምሩ ብር 7,819,068.22 አላግባብ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡--

ሠንጠረዥ-9 አላግባብ የተፈፀመ ክፍያ ፣

ተ/ቁ	ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት	2012 ሂሣብ			2013 ሂሣብ		
		የመ/ቤት ብዛት	ገንዘብ ልክ	%	የመ/ቤት ብዛት	ገንዘብ ልክ	%
1	የክልል መ/ቤቶች	27	4,246,966.67		7	1,163,714.68	
2	ባሕር ዳር ከተማ						
3	ምዕ/ጎጃም	9	663,668.93		3	49,382.60	
4	ምስራቅ ጎጃም	5	234,939.04		6	2,200,320.49	
5	ማዕከላዊ ጎንደር`	2	29,700.00		2	82,550.84	
6	ሰሜን ጎንደር	2	35,113.03		3	158,452.71	
7	ምዕራብ ጎንደር				1	43,539.23	
8	ደቡብ ጎንደር	6	1,868,954.20		5	1,891,064.27	
9	አዊ ብሔረሰብ	3	77,571.97		6	1,850,158.76	
10	ደቡብ ወሎ	16			1	45,537.20	
11	ኦሮሞ ብሔረሰብ	5	950,232.81				
12	ሰሜን ሸዋ	15	633,957.27		4	334,347.44	
13	ሰሜን ወሎ	12	1,693,906.15				
14	ዋግኽምራ ብሔ/	4	369,892.09				
	ድምር	106	12,443,844.63		38	7,819,068.22	

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው አላግባብ ከተከፈለው ክፍያ ከብር 150,000.00 በላይ ድርሻ ከሚይዙት መ/ቤቶች መካከል፡-

- **ምስራቅ ጎጃም ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 2,100,575.64** የጎጃም ባህል ማዕከል የአዳራሽ ግንባታ 2ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም ከተሰራ ስራ በላይ በብልጫ የተፈፀመ ክፍያ፣
- **እንጅባራ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,507,166.65** የአገልግሎት ጽ/ቤት አንድ ግሪደር ከእነሙሉ መለዋወጫው ከመንግስት ግዥ ንብረት ማስወገድ ኤጀንሲ ግዥ እንዲፈፀምለት በጠየቀው

መሰረት የግሪደር ግዥው ተፈጽሞ ሲቀርብ የመለዋወጫ እቃ ግዝው ሳይቀርብ ብልጫ የፀደቀ ክፍያ፣

- **አዲስ ዘመን ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 1,452,514.67 ከቀበሌ 02 ከአዲስ አበጀ እስከ ስመኘው ወርቁ ድረስ ያለው የኮብል እስቶን መንገድ ቆረጣ ንጣፍ ዲች ስራ 3ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም፣ከቀበሌ 03 ከዳሳሽ እስከ ዶክተር አደራጀው ድረስ ያለው የኮብል እስቶን ንጣፍ ስራ 1ኛ እና 4ኛ ዙር ክፍያ፣ከቀበሌ 02 ከቴሌ እስከ አዲስ አበጀ ድረስ ያለው የውሃ ማፋሰሻ ግንበታ 3ኛ እና 4ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም መከፈል ከነበረበት በላይ በብልጫ የተከፈለ ክፍያ፣
- **አብክመ መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ ብር** 1,006,856.64 በባህር ዳር ከተማ የአሮጌው መናህሪያ ግንባታ 7ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም፣
- **ስማዳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 377,754.30 የትምህርር ጽ/ቤት ሰራተኞች ለልምድ ልውውጥ ባህር ዳር ከተማ ሳይሄዱ የተከፈለ ውሎ አበል፣
- **ጓንጓ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 286,707.22 የግብርና ጽ/ቤት ለሚያሰራው የንብረት ክፍል ግንባታ 1ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተፈፀመ ክፍያ፤ስፖርት፣አስተዳደር ጽ/ቤት፣ፖሊስ ጽ/ቤት እና ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት መስክ ለሄዱ ሰራተኞች ውሎ አበል ክፍያ ሲፈጽም ከቆይታ ጊዜ በላይ በብልጫ የተከፈለ፣ከባህል ቱሪዝም ጽ/ቤት ከመደበኛ በጀት ክፍያ ሲፈፀም የአራሹ ባህል ቡድን ከምነው ሸዋ ኢንተርቴይመንት ጋር ካሴት ለማሳተም ውል የያዘ ቢሆንም ላልታተም ካሴት የተፈፀመ ክፍያ፣በሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት ግቢ ውስጥ በመደበኛ ሂሳብ ለሚገነባው የቢሮ ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ፣
- **ሞረትና ጅሩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 195,812.37 የወረዳው ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ሰራተኞች መስክ ለመጡት ክፍያ ሲፈፀም ከታሪፉ በላይ የተከፈለ፣የቴክኒክና ሙያ ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤት የወርክሾፕ ማስፋፊያ ክፍያ ሲፈፀም ከቅድሚያ ክፍያ ያልተመለሰ፣ከገንዘብ ጽ/ቤት፣ ከአስተዳር ጽ/ቤት፣ከጤና ጥበቃ ጽ/ቤት፣ከዋሽ እና ከጤና ተራድኦ ሂሳብ ለሰራተኞች ውሎ አበል ክፍያ ሲፈፀም ከቆይታ ጊዜ በላይ በብልጫ የተከፈለ እና በድጋሚ የተከፈለ ውሎ አበል፣የግብርና ጽ/ቤት፣ትምህርት ጽ/ቤት፣እንስሳት ሀብት ልማት ጽ/ቤት እና የአስተዳደር ጽ/ቤት ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ አላግባብ የተከፈለ የነዳጅ ሂሳብ፣

የ2013 በጀት ዓመት አላግባብ የተከፈለ ክፍያ ብር 7,819,068.22 ከ2012 በጀት ዓመት ብር 12,443,844.63 ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት ቁጥር በ68 በገንዘብ መጠን ደግሞ በብር 4,624,776.41 ቀንሶ ተገኝቷል፡፡ አላግባብ ከተፈጸመው ክፍያ የተተካ ገንዘብ ስለመኖሩ ይህ ጥንቅር እስከተሠራበት ሰኔ 24/2014 ዓ.ም ድረስ ለመ/ቤታችን አልተገለጸም፡፡

1.8.3. የግንባታ ስራዎች ወጪን በተመለከተ፤

ማንኛውም የግንባታ ክፍያ በውሉና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት በባለሙያ እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው የግንባታ ክፍያ አፈፃፀም መመሪያን ባልተከተለ መንገድ በ8(8%) መ/ቤቶች በድምሩ ብር 5,401,665.39 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

ከዚህም ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት መ/ቤቶች፡-

- ምስራቅ ጎጃም ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል የጎጃም ባህል ማዕከል እና የመሰብሰቢያ አዳራሽ ግንባታ ለተከናወነበት ክፍያ ሲፈፀም ከውለታ በላይ የተፈፀመ ክፍያ ብር 3,895,855.98፣
- ጓንጓ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል የወረዳው የእንስሳት ሀብት ልማት ጽ/ቤት እና ሴቶችና ህፃናት ጽ/ቤት የህፃናት ማቆያ ግንባታ 1ኛ፣2ኛ እና 3ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም የስራ ስፍር ልኬታ ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ ብር 709,326.37፣ናቸው፡፡

እነዚህ ከብር 250,000.00 በላይ ስራው ስለመከናወኑ የሚያሳዩ የስራ ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ እና ለተሰራው ስራ ተጨማሪ የስራ ውለታ ሳይያዝ ክፍያ ተፈፃሞ የተገኘባቸው ሲሆኑ ሥራው በትክክል በስራ ዝርዝሩ እና በውለታው መሰረት ስለመሠራቱ በገለልተኛ የምህንድስና ባለሙያ እንዲረጋገጥ ሆኖ ያልተሰራ መሆኑ ከተረጋገጠ ገንዘቡ ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲደረግ እና ድርጊቱን በፈጸሙት ባለሙያዎች ላይ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባዉ በኦዲት ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡ የግንባታ ማስረጃ ሳይቀርብ ከተፈጸመው ክፍያ ውስጥ የተተካ ወይም ተገቢው ማስረጃ የቀረበለት ሂሳብ ስለመኖሩ ይህ ጥንቅር እስከተሠራበት ሰኔ 24/2014 ዓ.ም ድረስ ለመ/ቤታችን አልተገለጸም፡፡

1.8.4. ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ፤

ማንኛውም ክፍያ ተፈጽሞ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ ሲገባው ይህን በመተላለፍ በ7(7%) መ/ቤቶች የተለያዩ የዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈጸም ለተከፈለው ብር 2,331,294.71 የወጪ ደረሰኝ ወይም ፋክቱር ሳይቀርብለት ክፍያ ተፈጽሞና በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

ሠንጠረዥ-10 ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ፣

ተ.ቁ	ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት	2012 ሂሣብ			2013 ሂሣብ		%
		የመ/ቤት ብዛት	የገንዘቡ ልክ	%	የመ/ቤት ብዛት	የገንዘቡ ልክ	
1	የክልል መ/ቤቶች	3	3,577,029.66		3	1,957,015.91	
2	ባህር ዳር						
3	ምዕራብ ጎጃም	4	409,704.53				
4	ምሥራቅ ጎጃም	1	13,279.34				
5	ማዕከላዊ ጎንደር						

6	ሰሜን ጎንደር						
7	ምዕራብ ጎንደር						
8	ደቡብ ጎንደር	2	5,209,997.18		1	11,696.00	
9	አዊ ብሔረሰብ				1	18,412.90	
10	ደቡብ ወሎ	3	70,064.54				
11	ኦሮሞ ብሔረሰብ	2	79,089.50				
12	ሰሜን ሸዋ	2	80,876.17		2	344,169.90	
13	ሰሜን ወሎ	3	155,750.00				
14	ዋግሽምራ ብሔረሰብ	1	658,051.50				
ድምር		21	10,253,842.42		7	2,331,294.71	

በአጠቃላይ ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ ካለፈው ዓመት ብር 10,253,842.42 ጋር ሲነፃፀር በ2013 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በቁጥር በ14 እና በገንዘብ መጠን ደግሞ በብር 7,922,547.71 ቀንሶ ተገኝቷል፡፡ ይህም በማስረጃ አቀራረብ ዙሪያ መ/ቤቶች ገና ከችግሮቻቸው እንዳልተላቀቁ የሚያመላክት ሲሆን የአብክመ ገጠር መገድ ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ ብር 1,082,202.91 በመያዝ በማስረጃ አቀራረብ ዙሪያ ችግሩ ገዝፎ የታየበት መ/ቤት ነው፡፡

ስለሆነም ክፍያውን የፈፀሙት መ/ቤቶች በከፈሉት ገንዘብ ልክ ተገቢውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ማግኘታቸውን የማያመላክት በመሆኑ ለእያንዳንዱ ክፍያ ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ እንዲያያዝ ወይም ያለማስረጃ የተከፈለው ገንዘብ ከሚመለከተው ላይ ተመላሽ እንዲሆን ለየመ/ቤቶች በፃፍነው ሪፖርት ያሳሰብን ቢሆንም በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 24/2014 ዓ.ም ድረስ የሚያሳይ ግብረ መልስ አልደረሰንም፡፡

1.8.5. ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ የወጪ ማስረጃዎች፣

ክፍያዎች በተገቢው ማስረጃ ተደግፈውና መ/ቤቱ ለተጠቀመበት ዕቃና አገልግሎት በትክክል ስለመዋላቸው በኦዲት ለማረጋገጥ ክፍያ የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ተሟልተው ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ2(2%) መ/ቤቶች ብር 94,298,438.29 የያዙ የወጪ ማስረጃዎች ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ ሲሆን ከኦዲት በኂላ ማስረጃ ቀርቦ በውስጥ ኦዲተር ተረጋግጦ በግብረ መልስ እንዲገለጽ ብናሳስብም ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 23/20132 ዓ.ም ድረስ የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ምላሽ ባለመምጣቱ ግኝቱ ያለበትን ሁኔታ ማወቅ አልተቻለም፡፡

አዩ ጓጉሳ ወረዳ ብር 92,468,332.11 እና ምስራቅ እስቴ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 1,830,106.18 የወጪ ቫውቸሮች ከነደጋፊ ማስረጃዎቻቸው ለኦዲት ስራ ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

ማስረጃዎቹ ተገቢ ክፍያ እንደተፈፀመባቸውና ለማጭበርበር ወንጀል አለመዋላቸው ባለመረጋገጡ ስጋት ያስከተለ በመሆኑ ቀርበው የወጪው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥ ከማድረግ በተጨማሪ ሰነዶቹን የሰወሩ/ማቅረብ የነበረባቸው ሠራተኞች በህግ ተጠያቂ እንዲሆኑ በኦዲት ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

1.8.6. የግዥ ስርዓትን ያልተከተለ የወጪ ሂሳብ ፤

የዕቃና አገልግሎት ግዥ አፈፃፀም በስራ ላይ ባለው የዕቃና አገልግሎት ግዥ መመሪያ መሰረት ስለመፈፀሙ እንዲሁም የተሻለ የዕቃ ጥራትና የዋጋ ቅናሽ ለመገኘቱ እና የግዥ አፈፃፀም ሂደቶች የተሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ25(18%) መ/ቤቶች ብር 19,377,087.73 ዋጋ ያላቸው ግዥዎች የግዥ አፈፃፀም ስርዓት የሚጠይቀውን መስፈርት ሳያሟሉ ተከናውነው ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም ከዚህ በሚከተለው ሁኔታ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ-11 **የግዥ ስርዓትን ያልተከተለ፣**

ተ.ቁ	ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት	2012 ሂሣብ			2013 ሂሣብ		
		የመ/ቤት ብዛት	የግንዘብ ልክ	%	የመ/ቤት ብዛት	የግንዘብ ልክ	%
1.	የክልል መ/ቤቶች	24	27,021,129.56		10	14,549,731.62	
2.	ባህር ዳር						
3.	ምዕራብ ጎጃም	3	5,811,758.92		2	1,199,951.90	
4.	ምስራቅ ጎጃም	4	2,668,715.29		3	980,681.44	
5.	ማዕከላዊ ጎንደር	3	683,929.93				
6.	ሰሜን ጎንደር				1	102,382.79	
7.	ምዕራብ ጎንደር				1	30,816.30	
8.	ደቡብ ጎንደር	2	175,763.04		3	1,240,056.67	
9.	አዊ ብሔረሰብ	1	775,517.50		2	575,932.45	
10.	ደቡብ ወሎ	6	2,301,467.88		1	169,800.00	
11.	ኦሮሞ ብሔረሰብ	1	744,738.41				
12.	ሰሜን ሸዋ	9	6,552,964.51		2	527,734.56	
13.	ሰሜን ወሎ	7	11,937,000.22				
14.	ዋግኽምራ ብሔረሰብ						
	ድምር	60	58,672,985.26		25	19,377,087.73	

የግዥ አፈጻፀም ችግሮች ጎልቶ የሚታይባቸው መ/ቤቶች፡-

- **አብክመ ገጠር መንገድ ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ ብር** 10,139,088.77 የተሽከርካሪ የመለዋወጫ እቃ ግዥ ሲፈፀም በግልጽ ጨረታ ዘዴ መፈፀም ሲገባው አሳማኝ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ በቀጥታ የግዥ ዘዴ የተፈፀመ፣
- **መካነ ሰላም ጠቅላላ ሆስፒታል ብር** 2,150,023.26 ለሆስፒታሉ አገልግሎት የሚው የመብራ እቃ ግዥ ሲፈፀም በሚመለከተው የፍትህ አካል የውል ስምምነቱ ተመርምሮ ሳይፀድቅ የተፈፀመ ግዥ ብር 2,094,065.00 እና አሳማኝ ምክያት ሳይኖር በቀጥታ የግዥ ዘዴ የተፈፀመ የመስተንግዶ ግዥ፣
- **ጃቢ ጠህናን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 1,097,054.56 ከአስተዳደር ጽ/ቤት የመኪና ጎማ እና የመኪና መለዋወጫ ግዥ ሲፈፀም በግልጽ ጨረታ መፈፀም ሲኖርበት አሳማኝ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ በውስን እና በቀጥታ ግዥ ዘዴ የተፈፀመ፣
- **ደብረ ታቦር ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ብር** 882,598.09 የጽ/መሳሪያ ግዥ ሲፈፀም በግልጽ ጨረታ ዘዴ መፈፀም ሲገባው አሳማኝ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ በውስን ጨረታ የተፈፀመ ግዥ፣
- **ጎንቻ ሲሶ እነብሴ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 823,938.20 በወረዳው እንስሳት ሀብት ልማት ጽ/ቤት የመድሀኒት ግዥ ሲፈፀም የግዥ መጠየቂያ ሳይቀርብ የተፈጸመ ግዥ፣
- **ስማዳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 775,767.53 በጤና ጥበቃ እና ገንዘብ ጽ/ቤት የመኪና መለዋወጫ ግዥ ሲፈፀም በግልጽ ጨረታ መፈፀም ሲኖርበት አሳማኝ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ በውስን እና በፕሩፎርማ ግዥ ዘዴ የተፈፀመ እና በግብርና ጽ/ቤት የግንባታ እቃዎች ግዥ ሲፈፀም አሳማኝ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ በውስን ጨረታ ግዥ ዘዴ የተፈፀመ፣
- **አብክመ ክልል ምክር ቤት ብር** 666,213.37 የመኪና ጎማ ግዥ ሲፈፀም ከተፈቀደው መጠን በላይ የተፈፀመ የጎማ ግዥ፣ለቢሮው ከተፈቀደው የሻይ ቡና በጀት በላይ ለመስተንግዶ የተፈፀመ ክፍያ፣
- **የአዊ ብሔረሰብ ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 505,298.00 የንግድ ስራ ፈቃዱ ከተሰረዘ አቅራቢ የተፈፀመ የመስተንግዶ ግዥ፣ዋና ዋናዎቹና ከብር 500,000.00 በላይ የግዥ አፈፃፀምን ያልተከተለ ግዥዎች የተገኘባቸው መ/ቤቶች ናቸው፡፡

ግኝቱ ሊከሰት የቻለውም የግዥ መመሪያውን በተገቢው መንገድ በሥራ ላይ ካለማዋል የተነሣ ገንዘቡ ተገቢዉን ዕቃ (አገልግሎት) ሳያስገኝ እና ፍትሃዊ ውድድርን ሳያስተናግድ ግዥ እየተፈፀመ እንደሆነ በማስገንዘብ ለወደፊቱ መ/ቤቶቹ ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በኦዲት ሪፖርቶች ብናሳስብም ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 24/2014 ዓ.ም ድረስ የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ግብረ መልስ አልደረሰም፡፡

የ2013 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገዉ የግዥ ሂሳብ ከ2012 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝት ብር 58,672,985.26 ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት ቁጥር በ35 የቀነሰ ሲሆን በገንዘብ መጠን ደግሞ በብር 39,295,897.53 ቀንሶ ተገኝቷል፡፡ ይህም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የግዥ መመሪያውን በመከተል በኩል ገና ከችግር እንዳልተላቀቁ ያመላክታል፡፡ (ዝርዝሩን አባሪ 2 ይመልከቱ)፡፡

1.9. የተከፋይ ሂሳብ ኦዲት ውጤት፤

1.9.1 በወቅቱ ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሣብ፤

የ2013 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ48 መ/ቤቶች ብር 542,086,781.29 የተከፋይ ዕዳ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ወቅት የፋይናንስ መመሪያውን ተከትሎ ሳይከፈል ተገኝቷል፡፡(ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል)፤

ሠንጠረዥ-12 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ፤

ተ.ቁ	ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት	2012 ሂሣብ			2013 ሂሣብ		
		የመ/ቤት ብዛት	የገንዘቡ ልክ	%	የመ/ቤት ብዛት	የገንዘቡ ልክ	%
1	የክልል መ/ቤቶች	35	277,727,738.93		15	54,250,693.30	
2	ባህር ዳር ከተማ	1	132,165,233.00		1	87,078,486.82	
3	ምዕራብ ጎጃም	7	41,664,781.28		7	33,846,022.03	
4	ምስራቅ ጎጃም	10	42,697,331.74		6	74,082,486.51	
5	ማዕከላዊ ጎንደር	2	42,878,927.47		1	149,470,738.24	
6	ሰሜን ጎንደር	1	28,852,873.84		2	12,083,933.38	
7	ምዕራብ ጎንደር	1	1,606,342.18		1	8,920,717.82	
8	ደቡብ ጎንደር	6	26,283,733.46		5	49,384,644.08	
9	አዊ ብሔረሰብ	3	9,961,477.00		8	63,480,101.69	
10	ደቡብ ወሎ	10	212,211,856.89				
11	ኦሮሞ ብሄረሰብ	2	8,383,215.50				
12	ሰሜን ሸዋ	15	57,185,331.45		2	9,488,957.42	
13	ሰሜን ወሎ	13	124,670,918.60				
14	ዋግኸምራ ብሔረሰብ	2	24,487,346.38				
		108	1,030,777,107.72		48	542,086,781.29	

በአጠቃላይ በወቅቱ ያልተከፈለ ወይም ወደ ተጣራ ሀብት መቀየር ያለበት የተከፋይ ሂሳብ ካለፈው ዓመት ብር 1,030,777,107.72 ጋር ሲነፃፀር በ2013 በጀት ዓመት ሂሣብ ላይ የተገኘው በመ/ቤቶች ቁጥር በ60 የቀነሰ ሲሆን በገንዘብ መጠን ደግሞ በብር 488,690,326.43 ቀንሶ ተገኝቷል፡፡ ይህም በወቅቱ ያልተከፈለ ዕዳ ክምችት ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የቀነሰ መሆኑን ያመላክታል፡፡

በወቅቱ ያልተከፈለ ከፍተኛ የተከፋይ ሂሳብ ከሚታይባቸው መ/ቤቶች መካከል ጎንደር ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 149,470,738.24፣እነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 110,237,012.00፣ደ/ማርቆስ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰማዕከል ብር 46,133,877.03፣ዚገም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 31,736,127.47፣እብናት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 27,557,958.87፣ፍኖተ-ሰላም ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 19,116,705.78፣ዳንግላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 16,834,284.32፣አብክመ ክልል ምክር ቤት ብር 15,961,842.47፣አብክመ መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ ብር 13,616,305.62፣እናርጅ እናውጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 12,645,362.78፣እንጅባራ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 10,792,014.42፣ዳባት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 10,417,886.12 እና ደ/ታቦር ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 10,238,199.00፣ ከብር 10 ሚሊዩን በላይ የተከፋይ ዕዳ ክምችት በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ ይሸፍናሉ፡፡

ተከፋይ ሂሳቦች የራሳቸው የተወሰነ የመክፈያ ወይም ወደ ተጣራ ሀብት የሚቀየሩበት ጊዜ ስላላቸው በመመሪያው መሠረት ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ብናሳስብም ይህ ዘገባ ጥንቅር እስከተሰራበት ሰኔ 24/2014 ዓ.ም ድረስ ተከፋይ ሂሳቡ ስላለበት ደረጃ የታወቀ ሁኔታ የለም፡፡

1.9.2 ተቀጽላ ሌጀር ያልዘጋጀለት ተከፋይ ሂሳብ፣

የ2013 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ5 መ/ቤቶች ብር 7,218,472.23 በመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለማን እና መቸ እንደሚከፈል የሚያሳይ የተከፋይ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡

ሠንጠረዥ-13 **ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት ተከፋይ ሂሳብ፣**

ተ.ቁ.	መ/ቤት ስም	የመ/ቤቱ ብዛት	የገንዘቡ ልክ	%
1	የክልል መ/ቤቶች	2	5,341,981.81	
2	ባህር ዳር			
3	ምዕራብ ጎጃም	1	1,152,260.61	
4	ምስራቅ ጎጃም			
5	ማዕከላዊ ጎንደር			
6	ሰሜን ጎንደር			

7	ምዕራብ ጎንደር			
8	ደቡብ ጎንደር	1	644,811.83	
9	አዊ ብሔረሰብ	1	79,417.98	
10	ደቡብ ወሎ			
11	ኦሮሞ ብሄረሰብ			
12	ሰሜን ሸዋ			
13	ሰሜን ወሎ			
14	ዋግኽምራ ብሄረሰብ			
	ድምር	**5**	**7,218,472.23**	

ከሠንጠረዡ መመልከት እንደሚቻለው የተከፋይ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር አለመዘጋጀትን በተመለከተ አብክመ ፖሊስ ኮሚሽን ብር 2,727,399.04፣ጎንደር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ብር 2,614,582.77 እና ደንበጫ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,152,260.61፣ ከ1,000,000.00 በላይ በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙ ናቸው፡፡

ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለትን ተከፋይ ሂሣብ በተመለከተ በጥቅሉ ስለተመዘገበ ገንዘቡ ለማንና መቼ እንደሚከፈል ገላጭ ባለመሆኑ በሥራ ላይ ያለውን የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት በመከተል በየጊዜው ክትትል እየተደረገ በየባለቤቱ ተለይቶ መመዝገብ ወይም ለሚመለከተው መከፈል ካልቻለም ወደ ተጣራ ሀብት መቀየር እንዳለበት በሪፖርታችን አስገንዝበናል፡፡

ከዚህ ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ ተቀጽላ ሌጀር የተዘጋጀለት ስለመሆኑ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ሰኔ 24/2014 ዓ.ም ድረስ በግብረ መልስ ስላልተገለፀ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አልታወቀም፡፡

1.10. የሂሳብ ሪፖርት ልዩነቶች፤

ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የበጀት ዓመቱ የሂሳብ ሪፖርት በትክክል የተዘጋጀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ልዩነቶች ተገኝተዋል፡፡

ሠንጠረዥ-14 የሂሳብ ሪፖርት ልዩነቶች፤

በማነስ/በብልጫ	ጥሬ ገንዘብ	ባንክ ሂሳብ	የገቢ ሂሳብ	የተሰብሳቢ ሂሳብ	የወጪ ሂሳብ	የተከፋይ ሂሳብ	ዝውውር	የተጣራ ሀብት
በማነስ				55,624,023.99				
በመብለጥ					55,624,023.99			

የ2013 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች በአመታዊ የሂሳብ ሪፖርቶቻቸው ላይ በየሂሳብ ዓይነቱ አላግባብ በማነስ እና በመብለጥ ሪፖርት የተደረጉ ሂሳቦች ተገኝተዋል፡፡ ይህም የክልሉንም ሆነ የአገሪቱን የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ በተገለጹት ሂሳቦች የገንዘብ መጠን በማዛባት ለውሣኔ ሰጪ አካላት የተሳሳተ መረጃ ሊሰጥ እንደሚችል ያመለክታል፡፡

ስለሆነም ማስተካከያው በየደረጃው ተደርጎ የተዛባው የሂሳብ ሪፖርት እንዲስተካከል በየኦዲት ሪፖርቶቻችን አሳስበናል፡፡ (ዝርዝሩን አባሪ 2 ይመለከቱ)፡፡

1.11 የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ኦዲት ውጤት፣

1.11.1 የንብረት ሂሳብ ኦዲት ማድረግ ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች፣

የመንግስት መ/ቤቶች በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003 አንቀጽ 53 እና በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 02/2003 እና ተያያዥ የህግ ማዕቀፎች አግባብ ንብረቶች በአግባቡ ተመዝግበው፤ ክትትል እየተደረገባቸውና በየዓመቱ ቆጠራ እየተከናወነ የንብረት ሂሳብ ለኦዲት ስራ ዝግጁ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በዚሁ መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት 100 መ/ቤቶች መካከል በ36(36%) መ/ቤቶች የንብረት ሂሳብን ኦዲት ማድረግ የሚያስችል አሰራር ሳይኖር ተገኝቷል፡፡ ንብረትን ኦዲት አድርጎ አስተያየት መስጠት ላለመቻሉ ምክንያቶች፤

- የቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ (የእቃ መቆጣጠሪያ ካርዶች) ባለመቋቋሙ እና ቢቋቋምም ምዝገባ በተሟላ መልኩ ባለመከናወኑ፣
- የንብረት ክፍል ሰራተኞች ሲቀያየሩ የተሟላ ርክክብ የማይደረግ በመሆኑና ርክክብ ሲደረግም የርክክቡ ቀን ተገልጾ በመዛግብቶችና የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኞች ላይ መለያ ምልክት አለማድረግና አለመፈራረም፤
- በንብረት ግምጃ ቤት ውስጥ ንብረቶች ለቆጠራ አመቺ በሆነ መልኩ በባህሪ፤በእድሜና በአገልግሎት አይነት ለይቶ አለማስቀመጥ፣
- የንብረት ክፍል ሰራተኞች ሲቀያየሩ በቆጠራ የሚገኘውን ብቻ ቆጥሮ ለተተኪዎች ከማስረከብ ውጭ ማስረከብ የሚገባቸውን ያህል ስለመሆኑ በውስጥ ኦዲተሮች በኦዲት ከተረጋገጠ በኋላ አለመሆኑ፤
- ንብረት ከመጋዘን ከወጣ በኋላም ቢሆን ሙሉ ለሙሉ ጥቅም ላይ እስኪውል ድረስ ሃብት መሆኑ ታውቆ አለመከታተል፤የአላቂና ቋሚ ዕቃዎች የየወሩ ከወጪ ቀሪ እየታወቀና እየተረጋገጠ የሂሳብ ሪፖርት አካል እንዲሆኑ አለመደረጉ የሚሉት ዋና ዋና ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም የተጠቀሱትን የንብረት አስተዳደር መሰረታዊ ችግሮች በማረም ሊከሰት የሚችለውን የመንግስት ሃብት ብክነት እንዳይኖር ተገቢው የንብረት አስተዳደር፤አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ በየመ/ቤቱ እንዲተገበርና እንዲጠናከር በየሪፖርቶቻችን አሳስበናል፡፡(ዝርዝሩን አባሪ 2 ይመልከቱ)፤

ምዕራፍ 2:- ያለፉት ዓመታት የኦዲት ውጤቶች እርምጃ አወሳሰድ

የክትትል ኦዲት ሪፖርት

2.1 እርምጃ ያልተወሰደባቸው ያለፉት ዓመታት የኦዲት ውጤቶች

የ2013 በጀት ዓመት ሂሳባቸው በመ/ቤታችን መደበኛ ኦዲት በተደረገ 100 መ/ቤቶች በተደረገው የክትትል ኦዲት የ2012 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ተደርገው በተገኙ ግኝቶች ላይ በተቋማት ያለው የማሻሻያ እርምት እርምጃ አወሳሰድ ሲጣራ በ4 መ/ቤቶች በተሰጠው የማሻሻያ አስተያየት መሰረት ይህ የጥንቅር ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ቀን ሰኔ 24/2014 ዓ.ም ድረስ የእርምት እርምጃ ያልተወሰደባቸው ያለፈው ዓመት የኦዲት ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡ ዝርዝሩም ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

2.1.1. የ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ የኦዲት ውጤቶች ላይ አስተያየት ቢሰጥባቸውም እርምጃ ሳይወሰድባቸው የተገኙ ግኝቶች፤

- ደባርቅ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ያላግባብ የተከፈለ የትራንስፖርት አበል ብር 91,230.90፣
- ዳንግላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ያላግባብ የተከፈለ የውሎ አበል ብር 5,004.00፣
- ደ/ታቦር ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል በብልጫ የተፈፀመ የግንባታ ክፍያ ብር 1,692,026.66 እና ያለውለታ የተፈፀመ የግንባታ ክፍያ ብር 130,227.24፣
- ፍኖተ ሰላም ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ባልተሰራ ስራ ተከፍሎ የተገኘ የግንባታ ወጭ ብር 48,056.93፣

በመሆኑም በድምሩ ብር 1,966,545.73 በ4 መ/ቤቶች የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደባቸው የ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ የኦዲት ግኝቶች በወቅቱ በተሰጠው የኦዲት ማሻሻያ አስተያየት መሰረት እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሜ እያሳሰብን የፋይናንስ ግልጽ አሰራርና ተጠያቂነት እንዲጠናከር መ/ቤታችን ከሚመለከታቸው የፍትህ አካላት ጋር በትብብር የሚሰራውን ተግባር አጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን የእርምት እርምጃ በማይወስዱ እንዲሁም ምላሽ በማይሰጡ አካላት ላይ አስፈላጊው ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

ምዕራፍ 3:- ያለፉት አምስት ዓመታት አፈፃፀም

3.1 የዕቅድ አፈፃፀም ከ2009-2013 በጀት ዓመታት

የዋና ኦዲተር መ/ቤት በተሰጠው ተግባርና ሃላፊነት መሰረት ካለው የሰው ሀይል ጋር የተጣጣመ የስራ መርሀ ግብር በማውጣት ከ2009 እስከ 2013 በጀት ዓመት ድረስ ያለው የ5 ዓመት እቅድ ክንውን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠኝጠረዥ-1፡- የአምስት አመት የዕቅድ ክንውን በአወቃቀር እርከን፤

ዓ/ም	በክልል (ማዕከል)		በዞን		ከተማ አስተ		በወረዳ		ድምር	
	ዕቅድ	ክንውን	ዕቅድ	ክንውን	ዕቅድ	ክንዉን	ዕቅድ	ክንውን	ዕቅድ	ክንውን
2009	106	99	14	13	65	62	153	145	338	319
2010	104	99	13	12	92	88	101	96	310	295
2011	115	103	12	10	71	62	108	95	306	270
2012	112	102	12	11	83	75	124	113	331	301
2013	78	40	16	6	40	34	122	58	256	138
ድምር	**515**	**443**	**67**	**52**	**351**	**321**	**608**	**507**	**1541**	**1323**

ከሠንጠረዡ መገንዘብ እንደሚቻለው የክልሉ የኦዲት ክንውን የ2009 ሂሳብ በጀት ዓመት በቁጥር የ319 መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት የነበረ ሲሆን የ2013 ሂሳብ በጀት ዓመት የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን ጨምሮ የ138 መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ማድረግ ተችሏል፡፡ ይህም በ2013 ሂሳብ በጀት ዓመት የኦዲት ሽፋን በአሁኑ ጊዜ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው 776 ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ቁጥር አንፃር ሲታይ 17.78% የደረሰ ሲሆን በ2009 በጀት ዓመት ከነበረው የኦዲት ሽፋን 56.74% መቀነስ አሳይቷል፡፡ የኦዲት ሽፋኑ ከበጀት አንጻር ሲታይ አጠቃላይ ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በጀት ለ2013 በጀት ዓመት በክልሉ ምክር ቤት ከታወጀው የወጭ በጀት አንፃር ሲለካ 34% እና ከገቢ እቅድ አንፃር 20% ላይ ደርሷል፡፡

በአጠቃላይ በ5 □መታት የ1541 መ/ቤቶች ኦዲት ለማድረግ ታቅዶ 1323/85.85%/ መ/ቤቶች ተከናውኗል፡፡ይህም በያልሉ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው 776 ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ጋር ሲነፃፀር እያንዳንዱ መ/ቤት በአማካኝ በየ1.70 ዓመት የኦዲት ሽፍን ያገኙ መሆኑን ያሳያል፡፡

መ/ቤታችን የኦዲት ሽፋንን ለማሣደግ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ከኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ብዛትና ለክልሉ ከሚመደበው በጀት አንፃር የተቻለውን ሽፋን እየሰጠ ቢሆንም የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ቁጥር በየጊዜው መጨመር፣የክልሉ በጀት ከዓመት ዓመት እያደገ መምጣቱ እና በዚህ በጀት አመት በክልሉ ባጋጠመው

የፀጥታ ችግር ምክንያት በተሟላ ሁኔታ ኦዲት ማድረግ ባለመቻሉ በታሰበው መሠረት በመ/ቤት ቁጥር ደረጃ ሽፋን እየተሰጠ አለመሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

ስለሆነም የአካልተሃድሶ ማዕከላት፣ፍርድ ቤቶች፣ኮሌጆች እና ማረሚያ ቤቶች ሂሣብ በየአቅራቢያቸው በሚገኝ የነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል ተጠቃሎ የሚያዝበት ሁኔታ እንዲጠናና ተግባራዊ እንዲሆን አስተያየታችንን እያቀረብን ይህ ተግባራዊ ቢደረግ በአብዛኛው ኦዲት ተደራጊ ተቋማት በየበጀት ዓመቱ የኦዲት ሽፋን እንዲያገኙ ያግዛል ብለን እናምናለን፡፡

3.2. ከ2009 -2013 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች፤

ከ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ጀምሮ ባሉት 5 ዓመታት ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች በተገኙ መረጃዎች መሠረት የዋናዋና ግኝቶች አማካይ ስሌት (Weighted-Average) ተሠርቶ የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል፡፡

ተ.ቁ	የኦዲት ግኝት	2009	2010	2011	2012	2013	ድምር	አማካኝ
1	የጥሬ ገንዘብ እና የንብረት ሂሳብ ጉድለት	19,608,421.05	3,470,452.30	252,137.96	9,198,998.71	2,275,716.10	34,805,726.12	6,961,145.22
2	የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት የገቢ ሂሣብ	46,020.00	1,455,423.90	0	2,348,398.76	44,307.00	3,894,149.66	973,537.42
3	የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት የወጭ ሂሣብ	2,521,677.58	26,537,407.04	9,484,900.60	11,118,146.21	1,990,635.99	51,652,767.42	10,330,553.48
4	ለግል ጥቅም የዋለ	51,592.44	0	0	0	0.00	51,592.44	51,592.44
5	አላግባብ የተከፈለ	44,222,087.64	7,869,866.10	5,678,736.69	12,243,844.63	7,819,068.22	77,833,603.28	15,566,720.66
6	ስርዓቱን ባልተከተለ መንገድ የተፈፀመ የግንባታ ወጪ	50,268,896.58	69,136,212.19	16,313,768.12	45,546,545.04	5,401,665.39	186,667,087.32	37,333,417.46
7	የግዥ ስርዓቱን ያልተከተለ	119,427,957.14	69,982,706.37	29,254,400.10	58,672,995.26	19,377,087.73	296,715,146.60	59,343,029.32
8	ማስረጃ ያልቀረበበት	25,179,267.38	75,726,827.04	10,571,713.53	10,253,842.24	2,331,294.71	124,062,944.90	24,812,588.98
9	ለኦዲት ሊቀርብ ያልቻለ ማስረጃ	45,622,027.66	50,006,652.65	23,289,728.40	3,891,232.15	94,298,438.29	217,108,079.15	43,421,615.83
	ድምር	**306,947,947.47**	**304,185,547.59**	**94,845,385.40**	**153,274,003.00**	**133,538,213.43**	**992,791,096.89**	**198,794,200.81**

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው የክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር በተዘረዘሩት ዋና ዋና ግኝቶች ድክመት ይታይበታል፡፡ ከላይ የተመለከቱት ግኝቶች እንደየባህሪያቸው ተቀራራቢነት አጠቃላይ አቅጣጫው በሚከተሉት ግራፎች ተመልክቷል፡፡

የጥሬ ገንዘብና የንብረት ጉድለት

የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ የሚመራው በአብክመ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003፤ ደንብ ቁጥር 89/2004፤ የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 4/2004 እና በዋና ኦዲተር መ/ቤት የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት የአሰራር ማንዋሎች መሰረት ነው፡፡ ጥሬ ገንዘብ በባህሪው ለተለያዩ ብክነቶችና አደጋዎች የመጋለጥ እድሉ ሰፊ በመሆኑ በጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት መደገፍ ይኖርበታል፡፡ ከውስጥ ቁጥጥር ስርአቶች አፈፃፀም አንፃርም ኦዲት ሲደረግ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት በየአመቱ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ይህን ኦዲት ለማረጋገጥ ደግሞ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ በመዝገብ (ሌጀር) ምዝገባ እየተካሄደ በበጀት አመቱ መጨረሻ ደግሞ በካዝና የሚገኝ ጥሬ ገንዘብ እና እንደ ጥሬ ገንዘብ የሚቆጠሩ ሂሳቦች የተሟላ ህጋዊ ቆጠራ መደረግና መመዛዘን ይኖርበታል፡፡ ከዚህ አንፃር መሰረታዊው የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎች ስለማይሟሉ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብን ኦዲት አድርጎ አስተያየት መስጠት የማይቻልባቸው ኦዲት ተደራጊ ተቋማት በየጊዜው ቁጥራቸው ቀላል አለመሆኑን ያመላክታል፡፡

የጥሬ ገንዘብና የንብረት ሂሳብ ጉድለት



ከግራፉ መገንዘብ እንደሚቻለው የጥሬ ገንዘብና የንብረት ሂሳብ ጉድለት የታየባቸዉ የኦዲት ዓመቶች በ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ብር 19,608,421.05 እና በ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ብር 9,198,998.71 ከአማካኙ ብር 6,961,145.22 በላይ በመሆን ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው ይገኛሉ፡፡ በ2013 በጀት ዓመት ያለው የጉድለት መከሰት አዝማሚያ የቀነሰ መሆኑን ያመላክታል፡፡

በግራፉ ከታየው ጉድለት ውስጥ በ2009 በጀት ዓመት የተተካ ብር 50,305.71 ሲሆን ብር 3,360,000.99 በፍታብሄርና በወንጀል ክስ ሂደት ላይ እንደሚገኝ፣በ2010 በጀት ዓመት የተተካ ብር 213,592.05 ሲሆን

ብር 1,204,145.97 በፍታብሄርና በወንጀል ክስ ሂደት ላይ እንደሚገኝ፣በ2011 በጀት ዓመት ብር 76,388.49 በክስ ሂደት ላይ እንዳለ፣ በ2012 በጀት ዓመት በፍርድ ቤት በክስ ሂደት ላይ ያለ ብር 4,447,186.42 እና በፖሊስ ምርመራ ሂደት ላይ ያለ ብር 1,132,398.79 ሲሆን በ2013 ሂሳብ በተገኘው ግኝት ላይ እርምጃ ስለመወሰዱ እስከ ሰኔ 24/2014 ዓ.ም ድረስ ምላሽ አልደረሰንም፡፡

የማጭበርበር ድርጊት የተፈጸመበት የገቢ ሂሳብ

የመንግስት ገቢ በወቅቱና በአግባቡ ተሰብስቦ ለታለመለት ዓላማ መዋል ያለበት ቢሆንም በ5 ዓመቱ ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ብር 44,307.00 በተጭበረበረ መንገድ ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡

የማጭበርበር ድርጊት የተፈጸመበት የገቢ ሂሳብ፤



ከግራፉ መገንዘብ እንደሚቻለው የማጭበርበር ድርጊት የተፈጸመበት የገቢ ሂሳብ የታየባቸዉ የኦዲት ዓመቶች በ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ ብር 1,455,423.90 እና በ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ብር 2,348,398.76 ከአማካኙ ብር 973,537.42 በላይ በመሆን ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው ይገኛል፡፡ በ2013 በጀት ዓመት ያለው የማጭበርበር ድርጊት የተፈጸመበት የገቢ ሂሳብ አዝማሚያ የቀነሰ መሆኑን ያመላክታል፡፡

የማጭበርበር ድርጊት ከተፈጸመበት የገቢ ሂሳብ ውስጥ በ2012 በጀት ዓመት በፍርድ ቤት በክስ ሂደት ላይ የሚገኝ ብር 21,570.00 እንደሆነ በወቅቱ የደረሰን ምላሽ ያመላከተ ሲሆን በ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ በተገኘው ግኝት ላይ እርምጃ ስለመወሰዱ እስከ ሰኔ 24/2014 ዓ.ም ድረስ ምላሽ አልደረሰንም፡፡

ባለፉት ዓመታት የገቢ ሂሳብ ኦዲት ወቅት የተስተዋሉት ዋና ዋና ችግሮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የገቢ ደረሰኞችን ከ--እስከ መዝግቦ አለማሰራጨትና የተሰራጨ ደረሰኝ በትክክል ተሰርቶበት ገንዘቡ ለሚመለከተው ገቢ መደረጉ ተረጋግጦ እንዲመለስ የሚደረገው ክትትል አናሳ መሆኑ፣
- ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ሲፈለጉ አለመቅረብ፤
- የገቢ ደረሰኞችን አበላልጦ ገቢ መሰብሰብና ከትክክለኛው ቁጥር ላይ ስርዝ ድልዝ ማድረግ፤
- ሰራተኞች በስማቸው ባወጡት ደረሰኝ መሰረት ገንዘብ ከተሰበሰበ በኂላ ሙሉ ለሙሉ ለሚመለከተው ዋና ገንዘብ ያዥ ወይም የባንክ አካውንት ፈሰስ ለማደረጋቸው ከስር ከስር ክትትልና ቁጥጥር አለመደረጉ የሰበሰቡትን ገቢ በእጃቸው ማቆየት ብሎም ለግል ጥቅም አውሎ መቅረት ፣
- ጠቃሚ የሆኑ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቶችን በማዳከም ለመንግስት ገንዘብ ብክነት የአሰራር ክፍተት መፍጠር፤ ለምሳሌ አንድ ሰው ደረሰኝ በስሙ ወጪ በማድረግ፤ የገቢ ደረሰኝ ራሱ በማዘጋጀት ፤ገንዘብ በመሰብሰብ፤ገቢን ራሱ መዝግቦ ለሚመለከተው ፈሰስ የማድረግ፤ በዚህ አሰራር ምክንያት ሁሉንም ስራ ደርቦ በመስራት (ቁጥጥር ሳይደረግበት) መፈፀሙ፣
- ደረሰኞችን (አንዱ ሕጋዊ ሌላው ሕገ ወጥ) ጎን ለጎን አሳትሞ በመጠቀምና ገቢ በመሰብሰብ በህገወጥ ህትመት የሰበሰቡትን ገቢ ለግል ጥቅማቸው ማዋል ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

እነዚህን እና በአጠቃላይ የገቢ አሰባሰብ በተለይም የደረሰኞችን ዝውውር (በህጋዊ ርክክብ፤ የደረሰኙን ከ---እስከ እና ሴሪ በመጥቀስ መመዝገብና ስራ ላይ የዋሉትን እየተከታተሉ ማስመለስ)፤ የገቢ አሰባሰብ ታሪፎችንና መመሪያዎችን በሚገባ ተግባራዊ በማድረግ የመንግስት ገቢን ሰብስቦ ለታቀደለት ዓላማ ለማዋል ዝግጁ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት የወጪ ሂሳብ



ከላይ በግራፍ እንደተመለከተው የማጭበርበር ድርጊት የተፈጸመበት ክፍያ የ5 አመቱ ሲነጻጸር የ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ ብር 26,537,407.04 እና የ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ብር 11,118,146.21 ከአማካኙ ብር 10,330,553.48 በላይ ከፍተኛዉን ድርሻ ይዘው ይታያሉ፡፡ በ2013 በጀት ዓመት የማጭበርበር ወንጀል የተፈፀመበት ሂሳብ የቀነሰ መሆኑ ያመላክታል፡፡

የማጭበርበር ድርጊት ከተፈጸመበት የወጭ ሂሳብ ውስጥ በ2012 በጀት ዓመት በፍርድ ቤት በክስ ሂደት ላይ ያለ ብር 766,159.10 እና በፖሊስ የምርመራ ሂደት ላይ የሚገኝ ብር 159,286.59 እንደሆነ በወቅቱ የደረሰን ምላሽ የሚያመላክት ሲሆን በ2013 ሂሳብ በተገኘው ግኝት ላይ እርምጃ ስለመወሰዱ እስከ ሰኔ 24/2014 ዓ.ም ድረስ ምላሽ አልደረሰንም፡፡

ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ



- ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ በ2009 ብር 51,592.44 ከአማካዩ ብር 22,495.99 በላይ በመሆኑ ከፍተኛ ብልጫ አለው፡፡ በመሆኑም በ2009 የመንግስት ገንዘብ ለግል ጥቅም የዋለ ግኝት የተገኘ ቢሆንም በ2013 በጀት ዓመት ችግሩ ያልተከሰተ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

አላግባብ የተከፈለ ክፍያ



- አላግባብ የተከፈዉ ክፍያ በ2009 በጀት ዓመት ብር 44,222,087.64 ከአማካዩ ብር 15,566,720.66 በላይ በመሆኑ ከፍተኛውን ድርሻ ይዞ ይገኛል፡፡ በ2013 በጀት ዓመት ክፍያዎችን አላግባብ የመፈፀም ድርጊት የቀነሰ መሆኑን ያመላክታል፡፡

ስርዓቱን ባልተከተለ መንገድ የተፈጸመ የግንባታ ወጭ



- ስርዓቱን ባልተከተለ መንገድ የተፈጸመ የግንባታ ወጭ በ2010 በጀት ዓመት ብር 69,136,212.19፣ በ2009 በጀት ብር 50,268,896.58 እና በ2012 በጀት ዓመት ብር 45,546,545.04 ከአማካዩ ብር 37,333,417.46 በመብለጥ ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው ይገኛሉ፡፡ ከዚህ አንፃር የ2013 በጀት ዓመት ስርዓትን ያልተከተለ የግንባታ አፋፃፀም ወጭ የቀነሰ መሆኑን ያመላክታል፡፡

የግዥ ስርዓቱን ያልጠበቀ ግዥ



የግዥ ስርዓቱን ያልጠበቀ ግዥ በመፈፀም በ2009 በጀት ዓመት ብር 119,427,957.14 እና በ2010 በጀት ዓመት ብር 69,982,706.37 ከአማካዩ ብር 59,343,029.32 በላይ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙ ሲሆን በ2013

በጀት ዓመት ግኝት ከአማካኙም በታች በመሆኑ የግዥ ስርዓቱን ያልጠበቀ የግዥ አፈፃፀም የቀነሰ መሆኑን ያሳያል፡፡

ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ



- ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ በ2009 በጀት ዓመት ብር 25,179,267.38 እና በ2010 በጀት ዓመት ብር 75,726,827.04 ከአማካዩ ብር 24,812,588.98 ከፍተኛ ብልጫ አላቸው፡፡ ነገር ግን በ2013 በጀት ዓመት የመንግስት ገንዘብ ያለበቂና አስተማማኝ ማስረጃ ክፍያ በመፈፀም በወጪ የማፅደቅ ተግባር የቀነሰ መሆኑን ያሳያል፡፡

ለኦዲት ሊቀርብ ያልቻለ ማስረጃ



ለኦዲት ሊቀርብ ያልቻለ ማስረጃ የ2009 በጀት ዓመት ብር 45,622,027.66፣የ2010 በጀት ዓመት ብር 50,006,652.65 እና የ2013 በጀት ዓመት ብር 94,298,438.29 ከአማካኙ ብር 43,421,615.83 ከፍተኛዉን ድርሻ ይዘው ይገኛሉ፡፡ በ2013 በጀት ዓመት ማስረጃዎችን በአግባቡ ይዞ ለኦዲት ስራ

ሲፈለጉ በማቅረብ በኩል መጨመሩን የሳያል፡፡ ስለሆነም የተጠናከረ የተጠያቂነት ስርዓት ሊበጅለት እንደሚገባ ያሳያል፡፡

በወጪ ሂሳቦች ላይ በአብዛኛው የሚስተዋሉ ዋና ዋና ግኝቶች፡

- በክፍያና ደረሰኞች ላይ ስርዝ ድልዝ ማድረግና ከቀረበ ማስረጃ /ደረሰኝ/ በላይ ሂሳብ አበላልጦ ማወራረድ፣
- ሰራተኞች በሚሰሩበት ከተማ ለተሰጠ ስልጠና ስልጠኛው ሌላ ቦታ እንደተሰጠ በማስመሰል ክፍያ መፈፀም፣ ሌሎች የወጪ ሰነዶችን በማዘጋጀት ክፍያ መፈፀም፣ከተለያየ ሂሳብ ላይ በተመሳሳይ ቀናት ውሎ አበል መክፈል፤ በስልጠና ያልተሳተፉ ሰዎች ስምን አካቶ መክፈል፤ከቦታው ታሪፍ በላይ እና በመደበኛ ስራ ላይ እያሉ ውሎ አበል መከፈል፤ የመስተንግዶ ወጪዎችን አስቀድሞ በውድድር የተመረጠ አቅራቢ አለመለየት፤የተሳታፊዎችን ማንነትና የሚገባቸውን መስተንግዶ ዓይነትና መጠን በግልጽና ይህንኑ በሚያሳይ ውሳኔ አለማስደገፍ፤ ለብክነት በር በከፈተ አሰራር መፈፀም፣
- የግንባታ የስራ ስፍ ልኬት፣የስራ ዝርዝር እና የክፍያ ምስክር ወረቀት ሳይቀርብ ክፍያ መፈጸም፣ በሂሳብ ስሌት ስህተት ክፍያ መፈፀም፣ቀደም ባሉ ዙር ክፍያዎች የተሰራንና ክፍያ የተፈጸመበትን በድጋሚ መክፈል፤ለስራው ከተያዘው ውል በላይ ያለተጨማሪ ውል ክፍያ መፈጸም፤
- ተገቢውን ስፔስፊኬሽን አዘጋጅቶ ወደ ግዥ አለመግባትና የጥራት ደረጃውን ያልጠበቀ ዕቃ/ንብረት ገዝቶ ገቢ ማድረግ፤(ስፔስፊኬሽን ተዘጋጅቶ ከነበረም ከዚያ ውጭ መረከብ፤
- አስቀድሞ የተጠቃለለ የግዥ እቅድ አለማዘጋጀት እና የግልጽ ጨረታ ዘዴን የመጀመሪያ ምርጫ አለማድረግ ብሎም የግዥ ዘዴዎችን በተጨባጭ ምክንያት ላይ ተመስርቶ አለመምረጥና የግዥ ዘዴው የተመረጠበትን ምክንያት መዝግቦ/ቃለ ጉባዔ ይዞ ለ3ኛ ወገን በተጨባጭ ማስረጃነት አለማያያዝ፤
- ተገቢ ማስረጃ (የግዥ ጥያቄ፤ የጨረታ ማስታወቂያ፤የተወዳደሪዎች ሰነድ፤ፕሮፎርማ፤ ቃለ ጉባዔ ውሳኔ፤ለፕሮጀክት ሥራ የክፍያ ሂሣብ ማረጋገጫ(Payment certificate) የንብረት ገቢ ደረሰኝ፤ የውል ሰነዶችን ወዘተ . . የመሳሰሉት) ተሟልተውና ተያይዞ ሳይቀርቡ ክፍያ መፈፀም፤
- ወጭ የተፈፀመባቸውን የወጭ ማስረጃዎች ለኦዲት ያለማቅረብ፣
- ላልተሰራ ስራ ሃሰተኛ የወጭ ማስረጃዎች በማዘጋጀት ክፍያ መፈፀም ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ምዕራፍ -4:- ማጠቃለያና የማሻሻያ አስተያየቶች፤

4.1 የማጠቃለያና የማሻሻያ አስተያየቶችን ከዚህ ቀጥሎ አቀርባለሁ!

ማጠቃለያ፣

1. በዚህ አጭር ሪፖርት በዝርዝር እንደተመለከተው በ2013 በጀት ዓመት ሂሳቦች ላይ በተደረገው ኦዲት የጥሬ ገንዘብና የንብረት ሂሳብ ጉድለት፣የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት ገቢ፣ የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት ወጭ፣ አላግባብ የተከፈለ ክፍያ፣ ስርዓቱን ባልተከተለ መንገድ የተፈፀመ የግንባታ ክፍያ፣ የግዥ ስርዓቱን ያልጠበቀ ግዥ እና ማስረጃ ያልቀረበለት ወጭ የግኝቱ ሁኔታ የቀነ ሲሆን ለኦዲት ሊቀርብ ያልቻለ ማስረጃ የግኝቱ ሁኔታ የጨመረ መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡

   በጥቅሉ ከ2009 እስከ 2013 ያሉት 5 በጀት ዓመታት ሂደቱ ሲገመገም በሁሉም ሂሳቦች ግኝቶች ላይ መሻሻል እየታየ መምጣቱን ያመላክታል፡፡

የጥሬ ገንዘብ እና የንብረት ሂሳብ በሚመለከት፤

- የ2013 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ 13 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 2,275,716.10 ጉድለት የተገኘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከቀድሞው ገንዘብ ያዦች ብር 2,229,960.14 በጉድለት ተገኝቷል፡፡
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ (ሰኔ 30) በጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ መከታተያ ሌጀር መሠረት መገኘት ያለበት እና በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሲነጻጸር በ3 መ/ቤት ብር 882,242.09 የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ውጤት ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በማነስ (ጥሬ ገንዘብ በማነስ) ተስተውሏል፡፡
- በ7 መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2013 ዓ.ም ላይ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ናቸው፡፡

የገቢ ሂሳብን በሚመለከት፤

- በ2 መ/ቤቶች ብር 44,307.00 የማጭበርበር ድርጊት ተፈጽሞ ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡
- በ1 መ/ቤት ብር 7,598,879.50 የተጨማሪ እሴት ታክስ ሳይሰበሰብ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፣
- የ2013 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ29 መ/ቤቶች ብር 569,589,919.15 ባለው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት በወቅቱ ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፣
- ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ተሟልተው እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ17(17%) መ/ቤቶች ብር 703,529,247.33 የያዙ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፣

የተሰብሳቢ ሂሳብን በሚመለከት፤

- የ2013 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረገ መ/ቤቶች ውስጥ በ48 መ/ቤቶች ብር 2,320,625,230.63 በወቅቱ በፋይናንስ የአሠራር ስርዓት መሠረት ሣይሰበሰብ (ሳይወገድ) ተገኝቷል፡፡
- የ2013 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረገት መ/ቤቶች መካከል በ7 መ/ቤቶች ብር **57,916,991.13** የመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመተላለፍ የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡

የወጪ ሂሳብን በሚመለከት፤

- በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረገት መ/ቤቶች መካከል በ7 መ/ቤቶች ብር 1,990,635.99 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡
- ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈፀሙ ስለመሆናቸው ሲጣራ በ38 መ/ቤቶች የተለያየ ዕቃና አገልግሎት ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ፣አላግባብ እንዲሁም የመስክ ስራ ላላከናወኑ ሠራተኞች የውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች በድምሩ ብር 7,819,068.22 አላግባብ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
- ማንኛውም የግንባታ ክፍያ በውሉ፣በሥራ ዝርዝሩ እና በስራ ስፍር ልኬት መሠረት በባለሙያ እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው የግንባታ ክፍያ መመሪያን ባልተከተለ መንገድ መጀመሪያ ከተያዘው የግንባታ ውል ጋር ባልተጣጣመ ሁኔታ በ8 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 5,401,665.39 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፣
- ማንኛውም ክፍያ በወጭ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ ሲገባው ይህን በመተላለፍ በ7 መ/ቤቶች የተለያዩ የዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈጸም ለተከፈለው ብር 2,331,294.71 የወጪ ደረሰኝ ወይም ፋክቱር ሳይቀርብለት ክፍያ ተፈጽሞና ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- ክፍያዎች በተገቢው ማስረጃ ተደግፈውና መ/ቤቱ ለተጠቀመበት ዕቃና አገልግሎት በትክክል ስለመዋላቸው በኦዲት ለማረጋገጥ ክፍያ የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ተሟልተው ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ2 መ/ቤቶች ብር 94,298,438.29 ስለ ክፍያው ትክክለኛነት የሚያስረዳ ደጋፊ ማስረጃ ሳይቀርብለት ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- የዕቃዎች አገልግሎቶች የግዥ ስርዓቱን ያልጠበቀ በ25 መ/ቤቶች ብር 19,377,087.73 ዋጋ ያላቸው ግዥዎች የግዥ ስርዓት የሚጠይቀውን መስፈርት ሳያሟሉ ተከናውነው ተገኝተዋል፡፡

የተከፋይ ሂሳብን በሚመለከት፤

- የ2013 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረገ መ/ቤቶች ውስጥ በ48 መ/ቤቶች ብር 542,086,781.29 በወቅቱ በፋይናንስ የአሠራር ስርዓት መሠረት ሣይከፈል ወይም ወደ ተጣራ ሀብት ሳይቀየር ተገኝቷል፡፡

- የ2013 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ5 መ/ቤቶች ብር 7,218,472.23 የመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመተላለፍ የተከፋይ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡

የንብረት አያያዝ፣ አጠባበቅና አጠቃቀምን በተመለከተ፤

- በበጀት ዓመቱ በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት 100 መ/ቤቶች መካከል በ36(36%) መ/ቤቶች የንብረት ኦዲት ማድረግ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

- **የማሻሻያ አስተያየት፤**

  በ2013 በጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርቶች ከተስተዋሉ ግኝቶችና ከላይ ከተሰጠው ማጠቃለያ ከክልል እስከ ወረዳ ባሉ የመንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስና ሌሎች ሀብቶችን አመራር ለማጠናከር የሚከተሉትን የማሻሻያ አስተያየቶችን እናቀርባለን፣

  በጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ላይ ቁጥጥሩን ማጠናከር ስለማስፈለጉ፤

  በኦዲት ስራው ከተስተዋሉ ግኝቶች መረዳት እንደተቻለው በአንዳንድ መ/ቤቶች የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በተለያዩ ምክንያቶች ማመዛዘን ያልተቻለ እና ኦዲት በሚደረጉ መ/ቤቶች የጥሬ ገንዘብ ጉድለት የተከሰተ ሲሆን ይህም የመንግስትን ገንዘብ ለብክነትና ለምዝበራ እየተዳረገ በመሆኑ በየመ/ቤቱ የሚገኙ ሥራ አመራሮችና የውስጥ ኦዲተሮች ለጉዳዩ ትኩረት ሊሰጡት ይገባል፡፡

  የገቢ ሂሳብ ማጭበርበሪያ ክፍተቶችን በአሠራር ስርዓት ስለመዘርጋት፤

  በገቢ ሂሣብ ላይ ለተከሰቱ የማጭበርበር ድርጊቶች ክፍተት የፈጠሩ አሠራሮችን እየፈተሹ በመድፈንና የፈጻሚዎችንና አመራሮችን አቅም በመገንባት የመንግስት ሃብትን በአግባቡ መሰብሰብ እንዲቻል ማድረግና የፍትህ አካላትም በአጥፊዎች ላይ ተገቢ የሆነ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል እንላለን፡፡

  የወጪ ሂሳብ ማጭበርበሪያ ክፍተቶችን በአሠራር ስርዓት ስለመዘርጋት፤

  በወጪ ሂሣብ ላይ ለተከሰቱ የማጭበርበር ድርጊቶች ክፍተት የፈጠሩ አሠራሮችን እየፈተሹ በመድፈንና የፈጻሚዎችንና አመራሮችን አቅም በመገንባት የመንግስት ሃብትን በአግባቡ ይዞ መጠቀም እንዲቻል ማድረግና የፍትህ አካላትም በአጥፊዎች ላይ ተገቢ የሆነ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል እንላለን፡፡

  የተሰብሳቢ ሂሳብ አያያዝ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓትን ማጠናከር ስለማስፈለጉ

  በኦዲት ውጤቱ መሰረት መረዳት እንደተቻለው በበርካታ መ/ቤቶች ተሰብሳቢ ሂሳቡ መቸ እንደተሰጠ፣ከማን እንደሚሰበሰብ እና ለምን እንደተሰጠ ምንጩን የሚያሳውቅ የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር እየተዘጋጀ ባለመሆኑ ይህም የመንግስትን ገንዘብ ለብክነትና ለምዝበራ የሚዳርግ በመሆኑ በየመ/ቤቱ የሚገኙ ሥራ አመራሮችና የውስጥ ኦዲተሮች ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው ሊሰሩበት ይገባል፡፡

የቋሚና አላቂ ዕቃዎች አያያዝና አጠባበቅ መጠናከር የሚገባው ስለመሆኑ፤

በአብዛኞቹ መ/ቤቶች የቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ ተቋቁሞ የማይሠራባቸውና በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ቆጠራ የማይከናወን በመሆኑ የንብረት አያያዝና አጠባበቅን ኦዲት አድርጐ አስተያየት መስጠት ያልተቻለ ስለሆነ መ/ቤቱቹ ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ በማቋቋምና በየጊዜው ቆጠራ እያከናወኑ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪው ጋር እያመሳከሩ ልዩነት ሲፈጠርም ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እየወሰዱ ሊሰሩ የሚገባ ሲሆን ይህን ተግባራዊ በማያደርጉ የየተቋሙ ሃላፊዎችና ሰራተኞች ስራን ባልተመቸ ሁኔታ መምራትና ለብክነት በር በመክፈት ድርጊት ሊጠየቁ ይገባል፡፡

የኦዲት ግኝቶች እርምጃ አወሳሰድና ማሻሻያ አስተያየቶች ትግበራ ሊጠናከር ይገባዋል፡፡

ኦዲት ተደራጊዎች በምላሽ አሰጣጣቸው እየወሰዱት ያለው እርምጃ በቂ ሆኖ ባለመገኘቱ መልስ በማይሰጡና እርምጃ በማይወስዱ፤ በኦዲት አገልግሎቱ እየተጠቀሙ ከዓመት ዓመት በማይሻሻሉ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ላይ በየደረጃው በሚገኙ የምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎችና የፍትህ አካላት አማካኝነት ክትትል ሊደረግበት እንዲሁም የኦዲት እርምጃ አወሳሰድ ክትትልና ድጋፍ ግብረ ኃይል በየደረጃው በማቋቋምና በማጠናከር የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ስርዓቱ ሊጠናከር ይገባል፡፡

ይህን ክትትልና ተጠያቂነት ለማጠናከር በመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዩች ቋሚ ኮሜቴ (Public Accounts Committee) በክልሉ ምክር ቤት ማቋቋም ያስፈልጋል፡፡

በየደረጃው የሚገኙ ም/ቤቶች ለየአካባቢያቸው በሚደርሰው የውጪ እና የውስጥ ኦዲት ሪፖርቶች በክልሉ ም/ቤት እንደሚደረገው ሁሉ በበጀትና የመንግስት ፋይናንስ ጉዳዩች ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት ለየም/ቤቱ ጉባኤ በአጀንዳነት ቀርቦ ውይይት ሊደረግበትና አቅጣጫ እየተሰጠበት ክትትሉ ሊጠናከር ይገባል እንላለን፡፡

በመጨረሻም የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት፣የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤዎች፣የበጀትና የመንግስት ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎች ኮሚቴዎች፣የፍትህ አካላትና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሥራ ሂደት ላደረጋችሁልን የስራ ትብብር እና የመ/ቤቱ ሠራተኞች ደግሞ በዚህ ሪፖርት ለተገኙት ውጤቶች ላሳዩት ታታሪነትና ላላቸው መልካም ስነ-ምግባር ከፍተኛ ምስጋና እያቀርብኩ ሪፖርቴን በዚሁ አጠቃልላለሁ፡፡

አመስግናለሁ!!

አማረ ብርሀኑ /ዶ/ር /

ዋና ኦዲተር

ሰኔ/2014